## ጅማ ዩኒቨርሲቲ


የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድኅረ-ምረቃ መርሃ-ግብር


# የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አዘገጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ (በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ተተኳሪነት)


በ

ይመኙሻል ቀለታ


በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ-ዘዴ የአርቲስ ማስትሬት ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ


ህዳር 2014

ጅማ፤ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አዘገጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ (በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ተተኳሪነት)

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የአርቲስ ማስትሬት ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

በ

ይመኙሻል ቀለታ

ዋና አማካሪ፡- ምህረት ሳዳም(ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡- አብዱ ራህማን ፋንታሁን

ህዳር 2014

ጅማ፤ኢትዮጵያ

**ጅማ ዩኒቨርስቲ**

**የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች)ና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**በማህበራዊ ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነ-ፅሑፍ ( አማርኛ) ክፍለ ትምህርት**

**የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር**

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘቶች አዘገጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ (በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በይመኙሻል ቀለታ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት፤**

ዋና አማካሪ .........................................ፊርማ.........................ቀን..................

ረዳት አማካሪ.........................................ፊሪማ.......................ቀን................

የውጭ ፈታኝ ...........................................ፊርማ.........................ቀን......................

የውስጥ ፈታኝ ..........................................ፊርማ.........................ቀን......................

## የአማካሪዎች ይሁንታ

ተማሪ ይመኙሻል ቀለታ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ተማሪ ስትሆን መመረቂያ ጥናቷን ከአማካሪዎቿ ጋር በትብብር እየሰራች የቆየች ስለሆነ ለተቋቁሞ መቅረብ የምትችል መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

ዋና አማካሪ ስም፡- -------------------- ፊርማ ------------------- ቀን ----------------

ረዳት አማካሪ ስም ፡- ------------------ ፊርማ---------------------- ቀን--------------

# የአጥኝዋ ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው አጥኚ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የግል ስራዎቼ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡ አለማቀፋዊ ተቀባይነት እንዳላቸው ልምዶች መሰረት በጥናቴ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መሳሪያዎችና ስራዎች በሙሉ በዋቢ መጽሐፍት ስር በማስቀመጥ ዋጋ ሰጥቼባቸዋለው፡፡

የአጥኝዋ ስም ፡ ይመኙሻል ቀለታ

ፊርማ ------------------

# ምስጋና

ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ መሳካት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ስህተቱን በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ምህረት ሳዳም(ዶ/ር) ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለው፡፡ በመቀጠል ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ ስሰራ ከጎኔ ሳይለየኝ ልጆቼን በመጠበቅና በመንከባከብ ድጋፍና እገዛ ላደረገልኝ ባለቤቴ ለሀብታሙ በላይነህ፤ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመለገስ ድጋፍ ላደረጉልኝ የትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ለአቶ ታምራት ከበደና ለአቶ መብራቱ በላይነህ፤ እንዲሁም በጽህፈት አገልግሎት ከጎኔ በመሆን እየረዳኝ ስህተቱን ሲያርምልኝ ለነበረ ወንድሜ አሸናፊ ጸደቀ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ በመጨረሻም ይህ ጥናት የተሳካ እንዲሆን መረጃ በመስጠትና ተገቢውን አስተያየት በመለገስ ክፍተቱን ለሞላችሁ ለሚዛን ቁጥር ሁለት መምህራንና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ ነው። ጥናቱ ገላጭ የምርምር ንድፍን የተከተለ ሲሆን በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አምስት መምህራን በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል። የተሰበሰበው መረጃ በአግባቡ ተደራጅቶ ትንተና ተደርጎበታል። ከመረጃዎቹ የተገኙት ውጤቶች የሚያመለክቱት የአንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብ ለመማር ማስተማሩ ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ ልምምድ አመቺ መሆናቸውን፤ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመጽሐፍ አቀራረብ ተገቢነት፣ የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜና ችሎታ እንዲሁም ዳራዊ እውቀታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን፤ የመማሪያ መጽሐፉ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንደተዘጋጁና የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን ለማስተማር እገዛ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። በአንጻሩ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ያለመጣጣም ችግሮች መኖራቸውን፣ አልፎ አልፎ ስለ መልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ መካተታቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።*

# የይዘት ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ ii

የይዘት ማውጫ ........ iii

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ........ 4

1.4.1. የጥናቱ ዓብይ ዓላማ ........ 4

1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ........ 4

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 5

1.7 የጥናቱ ውስንነት ........ 5

1.8 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች የአጠቃቀም ብያኔ ........ 5

ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ........ 6

2.3 የማንበብ ምንነት ........ 7

2.4. የማንበብ ክሂልን የማስተማር ዓላማ ........ 9

2.5. የንባብ ደረጃዎች ........ 9

2.5.1 ቅድመ ንባብ ተግባራት ........ 9

2.5.2.የንባብ ጊዜ ተግባራት ........ 10

2.5.3. የድህረ ንባብ ተግባራት ........ 10

2.6.የአንብቦ መረዳት ምንነት ........ 10

2.7. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ........ 11

2.8. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነትና ባህሪ 11
2.8.1.የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነት 12
2.8.2. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ባህሪ 13
2.9. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አደረጃጀት 14
2.10. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት 14
2.11. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 16
3.1. የጥናቱ ንድፍ 19
3.2 የጥናቱ አካላይ 19
3.3 የመረጃ ምንጮች 19
3.3.1 የናሙና አመራረጥ ስልት 19
3.3.2 የትምህርት ቤት እና የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ 19
3.3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ 20
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች 20
3.4.1. ሰነድ ፍተሻ 20
3.4.3. ቃለ መጠይቅ 20
3.5. የመረጃ አጠነቃቀርና አተናተን ስልት 21
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ 22
4.1. የመረጃ ትንተና 22
4.1.1. የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ዳራ 22
4.1.2. የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መረጃ 23
4.1.3. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የንባብ ክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ 23
4.1.4. አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና 23
4.1.5. የአንብቦ መረዳት ትምህርት የይዘቶች አቀራረብ ትንተና 32

4.1.6. መምህራን ስለ አንብቦ መረዳት መልመጃ አዘገጃጀትና አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ........ 33
4.1.7 የመምህራኑ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ........ 33
4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 34
5.ማጠቃለያ መደምደሚያና አስተያየት ........ 37
5.1. ማጠቃለያ ........ 37
5.2 መደምደሚያ ........ 37
5.3 አስተያየት ........ 38
ዋቢ መጽሐፎች ........ 39
አባሪዎች
አባሪ አንድ

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ ፡- 1. ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን አጠቃላይ መረጃ.................................23
ሰንጠረዥ ፡-2. በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባህርይ.........................26
ሰንጠረዥ፡-3. ለአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን አላማ የማሳካት ብቃታቸውን ለመፈተሽ  የተደረገ ቃለ መጠይቅ................................................28

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው ዕውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በማዳበርና ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች በማጎልበት በታላሚው ቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተቀረጸውን የትምህርት ይዘቶች ተማሪው ሊተገብሯቸው በሚችልበት መልኩ የቋንቋውን ዓብይና ንዑሳን ክሂሎች ለማስተማር የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

Richard(2001) እንደሚገልጹት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ማለት ተማሪው አስፈላጊውንና የታለመውን የቋንቋ ግብዓት እንዲለማመድ ለማስቻል ዕድሉን የሚፈጥሩ ዋነኛው የትምህርት መሳሪያዎች እንደሆኑና በቋንቋ ትምህርት መርሃ ግብር ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተቀዳሚ ተግባሩ የተማሪዎቹን የስነ ልሳንና የቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃትን ለማዳበር ይረዳ ዘንድ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጅ ጽሑፍ ነው በማለትSheldon ed(1987) ይገልጻሉ፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ለቋንቋ ትምህርት ግብ መምታት ጠንካራ የኃይል ምንጭ ናቸው፡፡ በተለይም በተጠቃሚዎች፣በአዘጋጆች፣በተማሪዎች፣በመምህራንና በማህረሰቡ ዘንድ ከፖለቲካዊ፣ ከኢኮኖሚያዊና ከማህበራዊ ጠቀሜታ አንጻር ያላቸው ተፈላጊነት ከፍተኛ ነው፡፡ Hutchison and Torres (1994) የመማሪያ መጽሐፎች በሚዘጋጁበት ወቅት በመጽሐፎቹ ውስጥ የሚካተቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት በተገቢው መንገድ የተደራጀ እና ጥሩ የአቀራረብ ሂደት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ቅደም ተከተሉን ትኩረት አድርገው መሆን አለበት፡፡ Ur (1996) የአንብቦ መረዳት ትምህርት በክፍል ውስጥ ለማለማመድ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ማቅረብና መመዘን የተለመደ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ግብ መቺ መሆን እንዲችሉና አቀራረቡ ምን መምሰል እንዳለበት ትዳስ (2009) Nuttal (1996) Grellet (1981) Davies (1995) ን በመጥቀስ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ሲዘጋጁ ባለነበበ ሰው ሊመለሱ እንደማይገባ፣ ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዝ መሆን እንዳለበት፣ የጥያቄዎቹ ቁጥር ሳይበዛና ሳያንስ በቂ መሆኑ

እየተረጋገጠ መዘጋጀት እንዳለበትና ጥያቄዎቹ የተገለጹበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ፣ የጠጠረና የከበደ መሆን እንደሌለበት ገልጸዋል፡፡

Lindsay and Knight (2006፣74) የሚመረጠው ርዕሰ ጉዳይና የቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ያነቃቃል ሲሉ፤ MC Donaugh and Show (2003፣3) በበኩላቸወ የቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት፣ የቀደምት እውቀታቸውን ከጽሁፍ ጋር ለማገናዘብና የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲገመቱ ለማስቻል እንደሚጠቅም ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የንባብ ጊዜ ተግባራት ላይ የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

የእነዚህ ምሁሮች ሀሳብ በአጠቃላይ ሲታይ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች መረጃዎችን በጥልቀት ለማግኘት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥሩ፣ ቀጥሎ የሚነበበውን ጽሑፍ ይዘት ለመተንበይ፣ የአንብቦ መረዳት ሁኔታዎችን ለመከታተል፣ የተነበበውን ከቀጣዩ መረጃ ወይም ከቀደምት እውቀት ጋር እንዲያዛምዱና እንዲያነቡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ትልቅ ሚና እንዳላቸው ነው፡፡ Williams (1990፣39) “የድህረ ንባብ ዓላማ የተነበበውን ምንባብ ማጠቃለልና ከተማሪዎች ጋር ማዛመድ ነው፡፡”ሲሉ፣ Celcemurcia (1991፣204) በበኩላቸው “ በድህረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው በአነበቡት ጽሑፍ ላይ በጥልቀት የሚወያዩበት ክፍል ነው፡፡” በማለት ሀሳቡን ያጠናክሩታል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርገው የታቀዱ የመማር ማስተማር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ገለጻዎችን መልመጃዎችንና ምሳሌዎችን ወዘተ አካትተው በመያዛቸው ተማሪው የታለመውን የትምህርት ግብዓት እንዲያገኙና ባገኙትም የቋንቋ ግብዓት አማካይነት ቋንቋውን እንዲለማመድና ብቁ እንዲሆን የሚያስችል ሰነድ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችም በሚዘጋጁበት ጊዜ የመመሪያ ግልጽነታቸው፣ ከክፍለ ጊዜው ይዘት ጋር የሚሰጠው ጊዜ የተመጣጠነ መሆኑ፣ የተማሪዎችን የብስለትና የክፍል ደረጃ ያማከለ ይዘት መሆኑ፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚያዳብርና ሶስቱ የንባብ ደረጃዎችን አካቶ የያዘ መሆኑ ተረጋግጦ ሊሆን ይገባል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝዋ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ካነሷሷት ምክንያቶች መካከል የሀጎስ (2009) እና ትዳስ (2009) ጥናት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀጎስ (2009) ‹‹ለሰባተኛና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁ አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የመምህራን አተገባበር ፍተሻ›› በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ውጤቱም መምህራኑ ለሁሉም የመልመጃ ጥያቄ አይነቶች እኩል ትኩረት ሰጥተው እንደማያሰሩ አረጋግጠዋል፡፡

ትዳስ 2009 ‹‹የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የምንባቦችን አመራረጥና አደረጃጀት፣የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት ተገቢነት ››በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደ ሚያመለክተው ለአንብቦ መረዳት ትምህርት የቀረቡት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ተገቢነት የጎደላቸው በመሆናቸው ክህሉን ለማጎልበት አያስችሉም፡፡ የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ በመሆኑም አጥኝዋ ከላይ የቀረበውን የአጥኝዎች ውጤት መነሻ በማድረግ በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አዘገጃጀትና አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያላት ፍላጎት ነው፡፡

በተጨማሪም አጥኚዋ ለአራት ዓመታት ያክል በተደጋጋሚ የአማርኛ መምህርት ሆና በምታስተምርበት ጊዜ የሚከተሉትን ችግሮች በማስተዋሏ ነው፡፡

- ❖ የተተኳሪው ክፍል ተማሪዎች ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን ማለትም የቅድመ ንባብ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ሲታዘዙ ተገቢ መልስ መስጠት አለመቻላቸው
  - ❖ በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አተገባበር ላይ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን
  - ❖ መጽሐፉን በምትፈትሽበት ጊዜ አንዳንድ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መመሪያ ለተማሪዎች ግልጽ ሆነው የተደራጁ አለመሆናቸውን በማስተዋሏ
  - ❖ መጽሐፍ በቅርብ ተሻሽሎ የወጣ በመሆኑና ከመፅሐፉ ጋር የተያያዘ ከዚህ ቀደም የተጠና በቂ ጥናት ላይኖር ይችላል ብላ በማሰቧ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

- በተተኳሪው የክፍል ደረጃ በቀረበው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ መልመጃዎች ሦስቱን የንባብ ትምህርት ትግበራ ደረጃዎች ያካተቱ ናቸውን?
- በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ግልጽ በሆኑ መመሪያዎች ቀርበዋልን?
- የተተኳሪው ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሻሻል አመቺ ናቸውን?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1. የጥናቱ ዓብይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2007 ዓ.ም ታትሞ በስራ ላይ በዋለው የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አዘገጃጀትና አቀራረብ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡

### 1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

- በተተኳሪው የክፍል ደረጃ በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ መልመጃዎች ሦስቱን የንባብ ትምህርት ትግበራ ደረጃዎች ማካተት አለማካተታቸውን መፈተሽ
- በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ግልጽ በሆኑ መመሪያዎች መቅረብ አለመቅረባቸውን መፈተሽ
- በተተኳሪው ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ለማሻሻል አመቺ መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብና አዘገጃጀት ፍተሻ የሚል ሲሆን፣ ውጤቱም ለቋንቋ ሥነ-ዘዴ ባለሙያዎች፣ ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆችና ለተመራማሪዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የትምህርት ይዘት አዘገጃጀትንና አቀራረብን በተመለከተ በመጽሐፉ ውስጥ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ

ጊዜ ጥያቄዎች መካተት አለመካተታቸውን በመፈተሽ ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች በሚገባ በመጠቆም ክፍተቱ እንዲሞላ መረጃ ይሰጣል

- ❖ በተተኳሪው ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ይዘት መመሪያ አቀራረብ ግልጽ ስለመሆኑና አለመሆኑ ለስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች መረጃ ይሰጣል
- ❖ ወደ ፊት በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኚዎች እንደ መነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጊዜ፣ በቦታና በርዕሰ ጉዳይ ላይ የተወሰነ ሆኖ በ2007 ዓ.ም በታተመው የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና አተገባበር ፍተሻ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ክልል በቤንች ሸኮ ዞን በሚዛን አማን ክፍለ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት በሚዛን ቁጥር- 2 ትምህርት ቤት በ2013 ዓ/ም የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን ብቻ ናቸው፡፡ በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በርካታ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ያካተቱ መልመጃዎች ቢኖሩም የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና የይዘት አቀራረብ ላይ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

አጥኝዋ ይህን ጥናት ስታከናውን በርካታ ችግሮች አጋጥሟታል፡፡ ካጋጠሟት ችግሮች መካከል በተተኳሪው ክፍል ውስጥ ከሚያስተምሩ ከአምስት የአማርኛ መምህራን ብቻ ቃለ መጠይቁም ሆነ ሰነድ ፍተሻው የተደረገ በመሆኑ የጥናቱን ውጤት ውስን አድርጎታል፡፡

## 1.8 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች የአጠቃቀም ብያኔ

- ❖ **የመማሪያ መጽሐፍ፡-** የመማሪያ መጽሀፍ የሚባለው የአንድ ትምህርት አይነት አጠ ቃላይ ይዘቶችን አካቶ የያዘ ጥራዝ ነው
- ❖ **የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ-** ሌሎች ክሂሎችን ሳይጨምር የአንብቦ መረዳት የይዘት መልመጃዎች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ማለት ነው
- ❖ **አዘገጃጀት፡-** የተዘጋጀውን የማስተማሪያ መሳሪያ የያዘው የትምህርት ይዘት

# ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተቀረጸውን የትምህርት ይዘቶች ተማሪው ሊተገብራቸው በሚችልበት መልኩ የቋንቋውን አብይና ንዑሳን ክሂሎች ለማስተማር የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው። Richard (2001) እንደሚገልጹት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ማለት ተማሪው አስፈላጊውንና የታለመውን የቋንቋ ግብዓት እንዲለማመድ ለማስቻል ዕድሉን የሚፈጥሩ ዋነኛው የትምህርት መሳሪያዎች እንደሆኑና በቋንቋ ትምህርት መርሃ ግብር ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ያብራራሉ።

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተቀዳሚ ተግባሩ የተማሪዎችን የስነ ልሳንና የቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃትን ለማዳበር ይረዳ ዘንድ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጅ ጽሁፍ ነው በማለት Sheldon ed (1987) ይገልጻሉ።

## 2.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አስፈላጊነት

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለቋንቋ ትምህርት ግብ መምታት ጠንካራ የኃይል ምንጭ ናቸው። በተለይም በተጠቃሚዎች፣ በአዘጋጆች፣ በተማሪዎች፣ በመምህራንና በማህረሰቡ ዘንድ ከፖለቲካዊ፣ ከኢኮኖሚያዊና ከማህበራዊ ጠቀሜታ አንጻር ያላቸው ተፈላጊነት ከፍተኛ ነው።Hutchison and Toress (1994)

ተስፋዬ (1993) የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት አስፈላጊነትን እንደሚከተለው ያስገነዝባሉ።

1. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ለመምህሩ የትምህርቱን ቅደም ተከተል ለመወሰንና በማቅረብ መነሻውንና መድረሻውን ለመጠቆምና ምን ማድረግ እንዳለበት በማመላከት ትምህርቱን ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲያስተምር እገዛ ያደርጋል።
2. የተለያዩ ጉዳዮችን በማቅረብ የሚፈጸሙ ስራዎችን በመወሰን፣ተማሪው የተማረውን በተግባር እንዲገልጽ ዕድል በመስጠት መምህሩም ሆነ ተማሪው ሊገነዘቡየሚችሉትን ይዘቶች በማቅረብ ትምህርቱ አስደሳች እንዲሆን ያደርጋል።
3. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት በቋንቋ ትምህርት ዘርፎች መካከል ያለውን ቅንጅት አጥጋቢ በሆነ ስልት ለማጣመር ያግዛል። ይህም የቋንቋውን ክሂሎች በተመጣጠነ ደረጃ ለማስተማር ከማገዛቸውም በላይ የቃላት አመራረጥን ፣ የአገባብ ስርዓትን፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምን፣ የአጻጻፍ ውበትን ወዘተ የሚያጠቃልሉ በመሆናቸው ጉልህ እገዛ ያደርጋሉ።

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርገው የታቀዱ የመማር ማስተማር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ገለጻዎችን መልመጃዎችንና ምሳሌዎችን ወዘተ አካትተው በመያዛቸው ተማሪው የታለመውን የትምህርት ግብዓት እንዲያገኙና ባገኙትም የቋንቋ ግብዓት አማካይነት ቋንቋውን እንዲለማምድና ብቁ እንዲሆን የሚያስችል ሰነድ መሆኑን ነው፡፡

## 2.3 የማንበብ ምንነት

ማንበብ ማለት የተፃፈን ወይም በጽሑፍ የሚገኙ ምልክቶችን የማየትና የመረዳት ሂደት ሲሆን እነዚህ ምልክቶችም ተቀናጅተውና ተደራጅተው ሰፋፊ አምዶችን ይመሰርታሉ፡፡ Williams (1990፣2):: አገላለጽ ደግሞ ንባብ ከአንድ ጽሑፍ ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር እንደመተርጎሚያ መንገድ የምንገልጽበት ነው፡፡ እንዲሁም Nuttal(1982፣2) ንባብ ፊደላትን መለየትና፣ መቁጠር ፣መነጠል፣ ድምጽን ማፍለቅ፣ ንበት፣ መናገርና አንድን ጽሑፍ መረዳት፣ትርጉምን መጨበጥ ወዘተ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ንባብ በአንድ ቃል መግለጽ እንደማይቻል ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ስለሆነም ንባብ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የተለየ ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል፡፡ "ንባብ ግላዊ ነው፡፡ ንባብ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚገኝን የአንድን ፀሐፊ መልዕክት በመከተል ምላሽ ለመስጠት የምንሞክርበት አዕምሮታዊ ተግባር ነው፡፡ ግላዊ ተግባርም ስለሆነም ለአነባቡም ሂደትና ለፀሐፊውም የሚሰጠውን ምላሽ ቀጥታ ላናስተውለው እንችላለን" ይላሉ፡፡ ከዚህም ንባብ አንድ ሰው በግሉ የሚያካሂደውን አዕምሮኣዊ ተግባር መሆኑን እንረዳለን፡፡

ይህም ንባብ በተለያየ መንገድ ሊገለጽ እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም፡፡ በተጨማሪም ስለ ማንበብ ምንነት በተመለከተ በመደበኛ የመማር ሂደት የሚዳብር መልዕክት ወይም ሃሳብ ወደ ድምፃዊ ቋንቋ የመተርጎም ስርዓት እንደሆነ፣ እንዲሁም ቃላትን ከማወቅና ከመተርጎም ጀምሮ ወደ ላቀ የማስተዋልና የማቀናበር ደረጃ እያደገ የሚሄድ የመገንዘብ ክንውን እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል Williams (1984፣52) በበኩላቸው ማንበብ የተፃፈን ነገር በመረዳት፣ በማመዛዘን፣ በመገመት በማመሳከር፣በመጠየቅ፣ በመመርመር፣ በመምረጥ በማወቅና በመርካት ላይ የሚመሰረት የመቀበያ ክሂል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን አንብቦ መረዳት የሚያካትታቸው ተግባራት የሚከተሉት እንደሆኑ በማያያዝ ያብራራሉ፡፡

**ሀ) የቃላትን ፍቺ መገንዘብ፡-** አንባቢው በፁሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አውዳዊ ፍቺ መረዳት ይኖርበታል።

**ለ) የፁሑፉን ግልጽ መልዕክት መገንዘብ፡-** አንባቢው በሚያነበው ፁሐፍ ውስጥ በግልጽ የሚታየውን መልዕክትና ይህንን ለማጉላትም ሆነ ለማጠናከር የገቡበትን ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት አለበት።

**ሐ) የጽሁፉን ድብቅ (ውስጣዊ) መልዕክት ማጤን፡-** አንድ አንባቢ በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ በግልጽ የሚታየውን መልዕክት ዋና ተግባሩ ቢሆንም በዚህ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም። በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት መነሻ በማድረግ በማገናዘብና በመመርመር የፁሑፉን ውስጣዊ መልዕክት መገንዘብ ይጠበቅበታል።

**መ) የአያያዞችን ሰዋሰዋዊ አገባብና ትርጉም መገንዘብ፡-** አንባቢው በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙትን አያያዞች አገባብና ትርጉም መገንዘብ ይኖርበታል። እነዚህን መገንዘብ የጽሁፉን መልዕክት ለመረዳት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

**ሠ) የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ ሀሳብ ፍሰት መረዳት፡-** አንባቢው ጽሁፍ ውስጥ ያሉትን የዓረፍተ ነገሮች ተናጠላዊ መልዕክት መረዳት ብቻ በቂ አይሆንም። የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለጽ አንዱን የዓረፍተ ነገር ከፊተኛውና ከተከታዮቹ ዓረፍተ ነገሮች ጋር ያለውን የሀሳብ ግንኙነት፣ የጽሁፍ የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርስ በርስ ተራክቦ ማስተዋል ይኖርበታል። አንድን ፁሁፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ማውጣት ወይም አንድን የቀረበ ጽሁፍ ከዳር እስከ ዳር ማንበልበል አይደለም። ማንበብ የመቀበያ ክሂል ሲሆን በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛና በውጭ ቋንቋ በመደበኛ የመማር ሂደት የሚዳብር አዲስ ክሂል ነው። እንደ ማዳመጥና መናገር ከቤተሰብና ከአከባቢ የሚለምዱት ሳይሆን በመደበኛ መማር ማስተማር ሂደት የሚዳብር ክሂል ከመሆኑም ባሻገር ግላዊ የአዕምሮ ተግባር መሆኑንም በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ። አንባቢው የቋንቋ ድምጾችንና የቃላት ንበት (አጠራር) ማለማመድ ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው በግልጽና በለሆሳስ የሚከናወን ነው። ከምሁራን ገለፃ መረዳት የሚቻለው ማንበብ እንደ ማዳመጥና መናገር ከቤተሰብና ከአከባቢ የሚለምዱት ሳይሆን በትምህርት ቤት የሚማሩት የመቀበያ ክሂል መሆኑን ነው። የማንበብ ክሂል በትምህርት የሚዳብር መሆኑ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል። ማንኛውንም ጽሑፍ የምናነብበት ምክንያት ይዘቱን ወይም ጭብጡን ለመረዳትና ለመገንዘብ ነው።

## 2.4. የማንበብ ክሂልን የማስተማር ዓላማ

በተለያዩ ምሁራን ከሚገለጹት የንባብ ክሂል የማስተማር ዓላማዎች መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን፡፡ የድምጾችን አነባበብ፣ መጥበቅና መላላት ለመለየት ፊደሎች እንዲሁም ቃላትና አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን ድምጽ በማሰማት ማንበብ ነዉ፡፡ Williams (1993) ይህንን ሀሳብ ሲያብራሩት ድምጽ በማሰማት ማንበብ ጠቀሜታ የሚኖረው በጀማሪነት ደረጃ ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ድምጾችና ፊደሎችን በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ለማረጋገጥ፤ ለሌሎች ተማሪዎች ደግሞ የተፃፈን ድምጽ፣ ፊደል ወይም ቃል ከሚነበበው ጋር ለማገናዘብ ሊያስችላቸው ይችላል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪው በትክክል ማንበብ ከቻለ በኋላ ድምጽ አውጥቶ ማንበብ ለግንዛቤ ጠቀሜታ እንደሌለው ይመከራል፡፡

## 2.5. የንባብ ደረጃዎች

### 2.5.1 ቅድመ ንባብ ተግባራት

በቅድመ ንባብ የሚቀርቡ መልመጃዎች ተግባራትና ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት፣ትኩረታቸውን ለመሳብ የሚያስችልና ስሜታቸውንና ገጠመኞቻቸውን መሠረት አድርጎ ከምንባቡ በፊት በቡድን፣ በጥንድና በግል ክንውን የሚቀርብ ተግባር ነው፡፡ ስለ ቅድመ ንባብ ሚና የተለያዩ ምሁራን ምሁራዊ ሃሳባቸውን የሰነዘሩ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ Lindsay and knight( 2006፣74) የሚመረጠው ርዕሰ ጉዳይ እና የቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ያነቃቃል ሲሉ፣ Mc Donaugh and show(2003፣3) በበኩላችው የቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት የቀደምት ዕውቀታቸውን ከጽሑፍ ጋር ለማገናዘብና የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲገምቱ ለማስቻል እንደሚጠቅም ያስገነዝባሉ፡፡ ከምሁራኑ ሀሳብ በመነሳት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችና ክንውኖችን ለምንና ስለምን እንደሚያነቡ ተገንዝበው ለተወሰነ ዓላማ የማንበብ ክሂላቸውን ለማዳበር ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም በቅድመ ንባብ ተግባር ከምንባቡ ይዘት ጋር የሚዛመዱ፣ ይዘቱን መተንበይ የሚያስችሉ፣ ለማንበብ የሚያነቃቁ ጥያቄዎችን በውይይት በማቅረብ ወደ ማንበብ ተግባር የሚያሸጋግሩ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.5.2.የንባብ ጊዜ ተግባራት

የንባብ ጊዜ ዓላማ ላይ የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል። የእነዚህ ምሁራን ሀሳብ በአጠቃላይ ሲታይ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች መረጃዎች በጥልቀት ለማግኘት ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥሩ ፣ ቀጥሎ የሚነበበውን ጽሁፍ ይዘት ለመተንበይ ፣ አንብቦ የመረዳት ሁኔታዎችን ለመከታተል፣ የተነበበውን ከቀጣዩ መረጃ ወይም ከቀደምት ዕውቀት ጋር እንዲያዛምዱ እና እንዲያነቡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ትልቅ ሚና እንዳላቸው ነው።
በአጠቃላይ ሲታይ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ በማንበብ ላይ እንዳሉ የሚሰሯቸው ጥያቄዎች ናቸው።

### 2.5.3. የድህረ ንባብ ተግባራት

በዚህ ደረጃ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች አንብበው የመረዳት ችሎታቸውን የሚያረጋግጡ ናቸው። የማንበብ ክሂልን ከማዳበር ጎን ለጎን ሌሎች ክሂሎችን የቋንቋ ክፍሎችን የመማሪያ መልመጃዎችን ያካትታሉ። ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ የሚሰሯቸው የእውነት ሀሰት ፣ የምርጫ ፣የቃላት የልዩ ልዩ ፍቺን የመፃፍና የማዛመድ፣ ንግግር የማድረግ፣ ሪፖርት የመፃፍ ወዘተ... መልመጃዎች የድህረ ንባብ ክንውኖች ናቸው።
ከላይ በቅድመ ንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ላይ የተሰነዘሩ አስተያየቶች እንደቀረቡት በድህረ ንባብ ተግባራትም ዙሪያ የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል። Williams (1990፣39) "የድህረ ንባብ ዓላማ የተነበበውን ምንባብ ማጠቃለልና ከተማሪዎች ዕውቀትና ዝንባሌ እና አተያይ ጋር ማዛመድ ነው።" ሲሉ፣ Celcemurcia (1991፣204) በበኩላቸው "በድህረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው ባነበቡት ጽሁፍ ላይ በጥልቀት የሚወያዩበት ክፍል ነው።" በማለት ሀሳቡን ያጠናክሩታል። በአጠቃላይ በቅድመ ንባብ ፣ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ ጊዜ የሚቀርቡ ጥያቄዎችና ክንውኖች የተማሪዉን አንብቦ የመረዳት ዓላማ ለማሳካት ነው።

## 2.6.የአንብቦ መረዳት ምንነት

እንደ Grellete (1991:3) አገላለጽ አንብቦ መረዳት ማለት ከሚነበበው ጽሁፍ አንባቢው የተፈለገውን መረጃ ማውጣትና መገንዘብ ሲችል ነው። ከዚህ ባሻገር Nuttal (1982:27) አንድ ተማሪ ወይም አንባቢ ጥሩ ተረድቷል የሚባለው ቢያንስ የሚያነበውን ፍሬ ሀሳብ ሰባ በመቶ መረዳት ሲችል ነው በማለት የአንብቦ መረዳት ደረጃ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ አሳይተዋል።

ከምሁራኑ ገለፃ በመነሳት አንብቦ መረዳት የአንባቢው ወይም የተማሪውን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ አዕምሮኣዊ ክንውን ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም በተፈጥሮ ይዘነው የምንወለድ ሳይሆን ተደጋጋሚ የንባብ ልምምድ የሚጠይቅና ትኩረት የሚሻ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ መቶ ፐርሰንት ባይሆንም በፁሑፍ መልክ የቀረበውን ምንባብ መገንዘብ ፣ ማመዛዘንና መገምገም መቻልን ይመለከታል፡፡

## 2.7. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች

በማንኛውም የቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎች አራቱን  የቋንቋ ክሂሎች ሰዋሰውንና  የቋንቋ ዕውቀት የሚያዳብሩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መልመጃዎች መካከል የአንብቦ መረዳት መልመጃ አንዱ ነው፡፡ የአንብቦ መረዳት ዓላማ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበርና ለማሻሻል እንደሆነ Nuttal (1996:118)  እንዲሁም Grellet(1991:4) ይገልፃሉ፡፡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የተለያዩ የጥያቄ ዓይነቶች ማካተት እንዳለባቸው ከዚህም አልፎ ተማሪዎቹ የንባብ ክሂላቸውን የሚያዳብሩባቸው መሆን እንዳለባቸው ምሁራኑ ገልፀዋል፡፡  የሚቀርቡት መልመጃዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን የንባብ ትምህርት ተማሪዎቹ እንዲገባቸው እና የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ እንዲረዱ እንጂ የተማሪዎቹን የምንባብ ችሎታ ለመመዘን ወይም ለመፈተን አይደለም፡፡ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው የተረዱትን መልዕክት በራሳቸው አባባል መግለጽ  እንዲችሉ መልመጃዎች ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

## 2.8. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነትና ባህሪ

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተማሪዎች ምንባቡን ምን ያህል አንብበው እንደተረዱት ለመገምገም የሚዘጋጁ ከመሆናቸውም ባሻገር የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ተማሪዎች እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የተለያዩ ምሁራን በሁለት ዓይነት ምድቦች ከፍለው ያስቀምጡዋቸዋል፡፡ የምድብ ምክንያታቸውን ስንመለከትም ከጥያቄዎቹ ማቅረቢያ መንገድ እና ካላቸው ውስብስብነት የሚመነጭ ነው፡፡ ከጥያቄዎቹ ማቅረቢያ መንገድ አንፃር ምርጫ ሰጭ ወይም ዝግ ጥያቄዎችና ድርሰታዊ ጥያቄዎች እንዲሁም ከባድ ወይም ውስብስብ ብለን እንከፍላቸዋለን፡፡ እነዚህንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 2.8.1.የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነት

#### 2.8.1.1. ምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች

እንደ Rivers (1981: 387), Atkins (1996:171-173), Nuttal (1982:128-133) ገለፃ ምርጫ ሰጭ ወይም ተጨባጭ መልስ ፈላጊ ጥያቄዎች ቀለል ያሉና የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚቀርቡ የጥያቄ ዓይነት ናቸው፡፡ በተለይ እነዚህ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማስታወስ አቅማቸውን ለማመልከት ይጠቅማሉ፡፡ በምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ስር የሚካተቱትን Nuttal (1982፡133) በሚከተለው መልክ ይከፋፍሏቸዋል፡፡

- አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ጥያቄዎች፡- ተማሪዎች ዓረፍተ ነገር እንዲያቀናብሩና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አይገደዱም፡፡ አዎ ወይም አይደለም እያሉ እንዲመልሱ ነው የሚጠበቀው
- መጠይቃዊ ጥያቄዎች ፡- በዚህ ጥያቄ ውስጥ የሚጠየቁ ይዘቶች የሚያካትቱት የሰው ስሞች፣ የቦታ ስሞች ፣ ድርጊቶች በጊዜ የሚገለፁ ነገሮችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በእነዚህ የጥያቄ ዓይነት የሚመደቡት የጥያቄ መጠየቂያዎች ማን?፣ ምን?፣ የትኛው? ፣ መቼ?፣ የሚሉትን ናቸው፡፡
- የምርጫ ጥያቄዎች፡-ተማሪዎች ለተሰጣቸው ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ይበልጥ መልስ የሚመልሳቸው ይሆናል ብለው የሚያምኑበትን ምርጫ ይወስናሉ፡፡ የምርጫ ጥያቄዎች የአማራጫቸው ብዛት አራት ወይም ሦስት አልያም ሁለት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የምርጫ ጥያቄዎች ተማሪዎች የመረጡት የምርጫ መልስ ለምን ትክክል መልስ እንደሆነ ወይም ለምን ስህተት እንደሆነ በመመርመር ሰፋ ያለ ትምህርት ያገኙበታል፡፡ ተማሪዎች የሚመርጡት መልስ ስህተት ቢሆንም እንኳ ከስህተታቸው ለመማር ትልቅ ሚና አለው፡፡
- የእውነት ሐሰት ጥያቄዎች፡- በዚህ የጥያቄ ዓይነት ተማሪዎች መልስ የማግኘትና የማጣት ዕድላቸው ሀምሳ ሀምሳ ነው፡፡
- የአዛምድ ጥያቄዎች፡- እነዚህ ጥያቄዎች በሁለት ጎናዊ ረድፎች የተደረደሩ ቃላትን፣ ሐረጎችን፣ ዓረፍተ ነገሮችን፣ ቁጥሮችንና ምልክቶችን ወዘተ የማዋሀድ፣ የማዛመድ፣ የማያያዝና የማቀናጀት ክንውኖች የሚፈፀምበት የጥያቄ ዓይነት ነው፡፡ ተማሪዎች ለሁሉም ጥያቄዎች ሊያጣምሩ የሚችሉ ጥንዶችን ይፈልጋሉ፡፡

#### 2.8.1.2. ድርሰታዊ ጥያቄዎች

ድርሰታዊ ጥያቄዎች ከምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ጋር ሲነፃፀሩ ከበድ ያሉ እና ውስብስብ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲያደራጁ፣ እንዲገልፁ ፣

እንዲያዋህዱ፣ የአረፍተ ነገሮችን ግንኙነትና ዝምድና እንዲያጤኑ፣አጠቃላይ የምንባቡን ሁኔታ እንዲገነዘቡ ሀሳባቸውን እንዲመርጡና እንዲገመግሙ የሚጠይቁ የጥያቄ ዓይነት ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ከምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች የሚለዩበት ሌላው መለያ ባህሪያቸው ተማሪዎች የመሰላቸውን ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ የማቅረብ ሚና አላቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በምንባቡ መነሻነት የግል አስተያየታቸውን እንዲሰጡ በምንባቡ ያሉ አገላለጾችና አቀራረቦች በራሳቸው አባባል እንዲያቀርቡ ነፃነት ስለሚሰጥ የተማሪዎችን የግል ብቃት ጎልቶ እንዲታይ የማድረግ ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በድርሰታዊ ጥያቄ የሚካተቱ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ምክንያታዊ ወይም ሀሳባዊ ጥያቄዎች፡- እነዚህ የጥያቄ ዓይነቶች የተሟላ መልስ ፈላጊ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም ለምንና እንዴት የሚሉትን የመጠየቂያ ብልሃቶች ይጠቀማሉ፡፡

### 2.8.2. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ባህሪ

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አንድን ንባብ ተከትለው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲሆኑ የጥያቄዎቹ ዓላማም ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መረዳት አለመረዳታቸውን ለመገንዘብና ለማወቅ እንጂ የምንባቡን ይዘት ለተማሪዎች ግልጽ እንዲሆን ለማስተማር የሚቀርብ አይደለም፡፡ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ይዘት መረዳት አለመቻላቸው የሚታወቀው ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች ሲመልሱ ነው፡፡ Nuttal (1982:125) Nunan (1989:33)፡፡ ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ ምን ያህል እንደ ተገነዘቡት ለማወቅ የሚቀርቡ ሲሆን ቅለት ክብደታቸው የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም Nuttal (1982:132) አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባ ባህሪያት እንደሚከተለው በየደረጃው ከፋፍለው ያስቀምጣሉ፡፡

1. **ተንታኝ ጥያቄዎች፡-** በዚህ አይነት የሚቀርቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ከሚቀርበው ምንባብ በቀጥታ ቃል በቃል በመውሰድ መልስ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡
2. **ማገናዘብና ማቀናበር የሚሹ ጥያቄዎች፡-** እንደ እነዚህ አይነት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከመጀመሪያው ከበድ ያሉ ናቸው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን ከምንባቡ በማውጣት የተጠቃለለ ሀሳብ እንዲያቀርቡ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ ያሉ ዓረፍተ ነገሮችን ለመገንዘብ አጠቃላይ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲረዱ የሚያደርጉ የመልመጃ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
3. **መመራመርን የሚሹ ጥያቄዎች፡-** በዚህ አይነት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን ደግመው በመስመር እንዲያነቡ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ ከላይ የተገለጹት የጥያቄ አይነቶች በጣም ከባድ የሚያደርጋቸው ተማሪዎች የምንባቡን አጠቃላይ

ሀሳብ በዝርዝር ለማግኘት የግድ ምንባቡን በጥልቀት እንዲመረምሩ የሚያደርጉ በመሆናቸው ነው፡፡

4. **የግምገማ ጥያቄዎች፡-** የዚህ አይነት ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው አጠቃላይ ፍሬ ሀሳቡን በመገንዘብ የራሳቸውን አስተያየት እንዲሰጡ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ በዚህ አይነት የሚቀርቡ መልመጃዎች የጸሐፊውን አቀራረብ፣ የምንባቡ ተአማኒነት፣ ስነ ጹሁፍም ከሆነ አቀራረቡን ይበልጥ ለመገምገም የሚያስችሉ የጥያቄ ባህሪይ ያላቸው ናቸው፡፡
5. **የግል አስተያየቶችን የሚጠይቁ ጥያቄዎች፡-** በዚህ አይነት የሚቀርቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ደራሲው ወይም ጸሐፊው የሰጠውን መልስ ለማንጸባረቅ የሚጋብዙ የተማሪውን የግል አስተያየትና አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች በየደረጃው ተዘጋጅተው ሊቀርቡ እንደሚገባ ነው፡፡ እነዚህ የሚመረጡ ይዘቶችም ከተማሪዎች አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ ሲሆኑ የአንብቦ መረዳት አላማውም ውጤታማ ይሆናል፡፡

## 2.9. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አደረጃጀት

ተስፋዬ (1995) ዓለም እሸቱና ሳህሉ አክሊሉ (1992፡11) ን ጠቅሰው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን በሁለት አብይት ክፍሎች መድበው አቅርበዋቸዋል፡፡ የምንባቡን አጠቃላይ የአቀነባበር ወይም የአደረጃጀት መንገድ እንዲገልጹ ማድረግ አንደኛው ክፍል ነው፡፡ በዚህ ስር የምንባቡን ተግባር የሚጠይቁ ማለትም መዘርዘራዊ፣ ቀስቃሽ ወይም ኪነታዊ፣ መሆኑን መለየት የሚጠይቁ ሆነው ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

ሁለተኛው ክፍል የምንባቡን ይዘት እንዲያብራሩና እንዲገልጹ  የሚያደርጉ ጥያቄዎች ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ደግሞ ግልጽ የሆኑና ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን መጠየቅ፣ በውስጠ ታዋቂነት የተገለጹ ጉዳዮችን በምንባቡ መሰረት መጠየቅ፣  በግምት ወይም በይምሰል ሊደረስባቸው የሚችሉትን ትርጉሞች መጠየቅ፣ በምንባቡ የቀረበውን ሀሳብ መገምገም፣ ማመዛዘን  የሚያስችሉ  ናቸው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ሲደራጁ የምንባቡን ተግባር፣ የምንባቡን  አይነት እና ይዘት በሚያብራራ መልክ ተዘጋጅተው ሊቀርቡ ይገባል፡፡

## 2.10. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት

እነዚህ መልመጃዎች የንባብ ትምህርት ከተከናወነ በኋላ የቋንቋ ክሂሎችንና ይዘቶችን መለማመድ እንዲሁም የተለያዩ የመማሪያ ዕውቀቶችን ለመቅሰም ይቻል ዘንድ የሚዘጋጁ

ተግባራት ናቸው፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አዘገጃጀት ወይም አቀራረብ በተለያዩ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- በምርጫ፣ በእውነት ወይም ሀሰት በል፣ በክፍት አጠያየቅ፣ ቅደም ተከተልን ማስተካከልና ሌሎችም ማቅረቢያ ዘዴዎች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ጥያቄዎቹ የሚቀርቡበት መንገድ የተለያዩ ሊሆኑ ቢችሉም እነዚህ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ግብ መቺ መሆን እንዲችሉና አቀራረቡ ምን መምሰል እንዳለበት የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ትዳስ (2009) Nuttal(1996) Grellet (1991) Davies( 1995)ን በመጥቀስ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ማዘጋጀት እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

- ጥያቄዎቹ ምንባቡን ባላነበቡ ሰው ሊመለሱ የሚችሉ ሊሆኑ አይገባም፡፡
- ጥያቄዎቹ በአንድ በተወሰነ የምንባቡ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ ሁሉንም የምንባቡን ክፍል በሚያስቡበት መንገድ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ሊመረመር ይገባል፡፡
- የጥያቄዎቹ ቁጥር ሳይበዛና ሳያንስ በቂ መሆኑ እየተረጋገጠ መዘጋጀት አለበት፡፡
- ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን አለባቸው፡፡
- ጥያቄዎቹ የተገለጹበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ፣ የጠጠረና የከበደ መሆን አይኖርበትም፡
- የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ተማሪው በደረጃው ሊኖረው ከሚገባው የቋንቋ ብቃት የሚልቅ የቋንቋ አጠቃቀም መጠቀም የለባቸውም፡፡
- ጥያቄዎቹ በአቀራረባቸው የተለያዩ የማቅረቢያ መንገዶችን ተከትለው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረው የሚቀርቡበትን መንገድ ማፈላለግ አስፈላጊ ነው፡፡

በተጨማሪም Connings worth (1995)ን በመጥቀስ መልመጃዎች በሚዘጋጁበትና በሚደራጁበት ወቅት ታሳቢ መሆን ያለባቸውን ጉዳዮች ገልጸዋል፡፡

- ግልጽ ከሆነ መመሪያ ጋር የሚቀርቡ መሆን መቻል አለባቸው፡፡
- ለመተግበር በቅድሚያ መመሪያዎቹን መከተል የሚያስችል ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- የማንበብ ክሂሎችን ማዳበር የሚያስችሉ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- መልመጃዎች ትምህርቱን ማጠናከሪያ እንጂ መገምገሚያ ብቻ መሆን የለባቸው፡፡
- ተተግባሪ ሊሆን ይገባል፡፡
- መልመጃዎች ሲቀርቡ አንድ የአቀራረብ መንገድ ብቻ መከተል የለባቸው፡፡

- ከሚመደበው የክፍለጊዜ ምጣኔ ጋር የተመጣጠኑ መሆን መቻል አለባቸው።
- ከተማሪው የቋንቋ አጠቃቀም አንጻር የተገናዘቡና ክሂሎችን አዋህደው የያዙ መሆን መቻል አለባቸው።
- የተማሪዎችን የዕድሜና የብስለት ደረጃ ያማከሉ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው።
- ከተማሪዎች ችሎታ አንጻር የተገናዘቡ መሆን አለባቸው።
- ተማሪዎችን ለስራ ወይም ለተግባር የሚገፋፉ ሳቢና ማራኪ መሆን አለባቸው።
- ለተማሪዎቹ ደረጃ የሚመጥኑ ዘዴዎች በመጠቀም የምንባብ ጥያቄዎች ሊቀርቡላቸው ይገባል።

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት የሚቻለው አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ መልመጃዎች በመጠናቸው በቂ፣ በአይነታቸው የተለያዩና ባላነበበ ሰው ሊመለሱ የማይችሉ መሆን እንዳለባቸው ነው። ከዚህ ባሻገር ጥያቄዎቹ የቋንቋ ክሂሎችን ሊያዳብሩ የሚችሉ እንዲሁም ጥያቄዎቹ በቃላት አጠቃቀም ከምንባቡ ከበድ ብለው መቅረብ እንደሌለባቸው በመጠኑ መገንዘብ ተችሏል።

## 2.11. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኝዋ ባደረገችው የቀደምት ጥናቶች ቅኝት በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች በአንድም በሌላ መንገድ ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ተገኝተዋል። እነዚህም ጥናቶች አማርኛን በማስተማር የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአዲስ አበባና በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የቀረቡ ናቸው። አጸደ (1999) "በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል በአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና ስልት ፍተሻ "በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው።

የጥናቱ ዋና ዓላማ በ1997 ዓ.ም ተሻሽለው በወጡት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ዓይነትና የአቀራረብ ስልት መፈተሽ ሲሆን ጥናቱ ገላጭ ምረምርን የተከተለ ነው። አጥኚዋ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመረጠቻቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሰነድ ምርምር፣ ምልከታ፣የቃለ መጠይቅና ለተማሪዎች የጹሑፍ መጠይቅ ናቸው። ከእነዚህም መረጃዎች የተገኘ ውጤትም በዚህ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ዝግጅት ወቅት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ረገድ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የማተኮር ሁኔታ ቢታይም ጥያቄዎችን በተመጣጠነ መንገድ ማዘጋጀቱ ላይ ግን ብዙ የሚቀሩ ነገሮች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል።

ሐጎስ (2009) በተወሰነ መልኩ ቢሆንም ከዚህ ጥናት ጋራ ተያያዥነት ያለው ጥናት አካሂዷል፡፡ ጥናቱ "ለሰባተኛና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁ አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የመምህራን አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዓብይ ዓላማ በሰባተኛና በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በቀረቡት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማዳበር የመምህራኑን አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመረጣቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ በዋናነት የጹሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ደግሞ በአጋዥነት የቀረቡ ናቸው፡፡ የተገኙትን መረጃዎች በመተንተን የተደረሰበት ውጤት መምህራኑ ለሁሉም የመልመጃ ጥያቄ ዓይነቶች እኩል ትኩረት ሰጥተው እንደማያሰሩ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

ሦስተኛው ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ትዳስ (2009) "የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የምንባቦችን አመራረጥና አደረጃጀት፣ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን አዘገጃጀት ተገቢነት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የምንባቦችን አመራረጥና አደረጃጀት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን አዘገጃጀት ተገቢነት መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሰነድ ፍተሻ፣ የጹሁፍ መጠይቅና የቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤትም በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች አመራረጥ የአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ምንባቦችን መምረጫ ከሆኑት መስፈርቶች አንጻር አብዛኞቹ ተገቢነት የጎደላቸው በመሆናቸው ክሂሉን ለማጎልበት አያስችሉም የሚል መደምደሚ ላይ ደርሳለች፡፡

ሌላኛው ይታያል (2003) ‹‹ የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሶስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ይዞት የተነሳው አላማ የአንብቦ መረዳት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ምን ይመስላል የሚል ሲሆን የተጠቀመው የጥናት ዘዴም ገላጭ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘም ውጤት እንደሚያመለክተው መምህራን የሚጠቀሟቸው የአንብቦ መረዳት አዕምሮአዊ ዕድገት ከማዳበሩ አንጻር በጣም ውስንነት እንደሚታይባቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡ይህ ጥናት አንብቦ መረዳትን መሰረት የደረገ መሆኑና አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀሙ ከዚህ ጥናት ጋር ቢያመሳስለውም አላማ፣ የክፍል ደረጃ ፣ጊዜና ቦታ ከዚህ ጥናት የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ከፍ ሲል በተለያዩ የሁለተኛ ዲግሪ ተመራቂ ተማሪዎች የቀረቡት ጥናታዊ ፁሁፎች በአጠቃላይ ሲታዩ ጥናቶቹ ያተኮሩባቸው የክፍል ደረጃዎች፣ የተካሄዱባቸው ክልሎች እንዲሁም የክፍል ደረጃቸው ምንም ግንኙነት የላቸውም። ነገር ግን በመረጃ መሰብሰቢያቸው ከፊል ተቀራራቢነት አሳይተዋል። የሀጎስ እና የትዳስ ጥናት ግን በርዕሰ ጉዳያቸውም ቢሆን ከዚህ ጥናት ጋር ከፊል ተቀራራቢነት ለማሳየት ሞክሯል። የሐጎስ (2009) የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ላይ ያተኮረ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር በከፊል ተመሳሳይነት ሲኖረው የሐጎስ ጥናት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የመምህራን አተገባበር ፍተሻ ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን የዚህ ጥናት ግን የመልመጃዎች አዘገጃጀትንም የሚፈትሽ በመሆኑ በከፊል ተመሳሳይነት አሳይቷል ይህ ጥናት ከሀጎስ ጥናት ጋር የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቱ በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት አለው። የሚያመሳስላቸውና የጋራ የሆነው ቃለ መጠይቅ ሲሆን የሚያለያያቸው ደግሞ ይህ ጥናት በዋናነት የመረጃ መሰብሰብሰቢያው ሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅ ሲሆን የሀጎሰ ጥናት ግን በዋናነት በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመው የጹሁፍ መጠይቅ ነው። በተጨማሪም ጥናቱ የተካሄደባቸው ቦታና ዓመተ ምህረት ይለያያሉ።

የትዳስ (2009) አጠቃላይ የምንባቡን አመራረጥና አደረጃጀት እንዲሁም የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት ተገቢነት ላይ መሆኑ፣ የዚህ ጥናት ትኩረት ግን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና አተገባበር መፈተሽ ላይ በመሆኑ በከፊል ተቀራራቢነት ሲኖረው በተጨማሪ በመረጃ መሰብሰቢያ ስልቱ ተመሳሳይነት አለው። ሌላው የትዳስ ትኩረት 10ኛ ክፍል መጽሀፍ ላይ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን የ5ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ላይ በመሆኑ ይለያል።

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች ውስጥ ከፊል ተቀራራቢነት ለማሳየት የሞከረው የሀጎስ፣የአጸደና  የትዳስ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ገላጭ የምርምርን ንድፍን የተከተለ ሲሆን በጥናቱ ዓላማ ላይ እንደተገለጸው በ2007 ዓ.ም በታተመው የአምስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና የክፍል ውስጥ አተገባበር ተገቢነት ተፈትሿል፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ለዚህ ጥናት የተጠቀመችው አይነታዊ ጥናት ነው ፡

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና የይዘት አቀራረብን መፈተሸን አላማ ያደረገ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በደቡብ ክልል በቤንች ሸኮ ዞን በሚዛን አማን ወረዳ በሚዛን ሙሉ አንደኛና ሁለተኛ ሳይክል የመጀመሪያ ደረጃ ቁጥር ሁለት ትምህርት ቤት ላይ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ አጥኚዋን ሊያጋጥሟት ከሚችሉ ች ግሮች አንጻር ምቹነት ስላለው መረጃዎችን በማግኘትና ተጠኚዎችን በቅርበት በመከታተል ረገድ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ በ2013 ዓ/ም የትምህርት ዘመን 5ኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ መምህራንና  ትምህርት ቤቱ አመቺ የንሞና ዘዴ በመጠቀም ተመርጧል፡፡

## 3.3 የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች  መማሪያ መጽሀፍና መምህራን ናቸው፡፡ በመሆኑም ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ  የተሰበሰቡ መረጃዎች በአስፈላጊው ቅደም ተከተል ተዘርዝረው በገለጻ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

### 3.3.1 የናሙና አመራረጥ ስልት

### 3.3.2 የትምህርት ቤት እና የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በሚዛን- አማን ክፍለ ከተማ በአጠቃላይ ስድስት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከስድስቱ ትምህርት ቤቶች፤ ሚዛን ቁጥር -2 ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም አጥኝዋ በዚህ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ የምትገኝ በመሆኑ  አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቅርብ ከመምህራን ማግኘት የምትችል መሆኑን በማመን ነው፡፡ ተተኳሪው ክፍል የተመረጠበት ምክንያት መጽሐፉ በቅርብ ተሻሽሎ የወጣ በመሆኑና ከዚህ ቀደም በዚህ መጽሐፍ ዙሪያ በቂ የተጠና ጥናት ላይኖር ይችላል ብላ በማሰቧ ነው፡፡ ስለሆነም የመማሪያ መፅሐፉ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ሊመረጥ ችሏል፡፡

### 3.3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በ2013 ዓ/ም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን የጥናቱ መረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ ከላይ በናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ አምስተኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር አምስት ብቻ በመሆናቸው አምስቱም በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጥናቱ ዓላማ ግብ ይመታ ዘንድ በዋናነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሰነድ ፍተሻ  ሲሆን በአጋዥነት ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካኝነት አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

### 3.4.1. ሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት በዋናነት መረጃ የተሰበሰበበት ሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ጥናቱ በ2007 ዓ.ም ዕትም የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብና አዘገጃጀት ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑ መልመጃዎቹ የሚገኙት በመጽሐፉ ውስጥ ስለዚህ    በመጽሐፉ ውስጥ የመመሪያዎች የአቀራረብ ግልጽነት፣ ተተግባሪነታቸውን፣ ከክፍለ ጊዜ ጋር ተመጣጥኖ የቀረቡ መሆናቸውን፣ የተማሪዎችን የዕድሜና የብስለት ደረጃ ያማከሉ መሆናቸውንና ሳቢና ማራኪ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስነድ ፍተሻ ለመረጃ መሰብሰበያነት አገልግሏል፡፡

### 3.4.3. ቃለ መጠይቅ

መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያገለግለው ቃለ መጠይቅ በ2007 ዓ.ም የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ላይ ያላቸውን አስተያየት ከመምህራን ለማሰባሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡ መረጃውን የሰጡት በ2013 ዓ/ም 5ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ብቻ ሲሆኑ መጠይቆቹ ከተደራጁ በኋላ በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተገምግሞ በኋላም በአማካሪው ማሻሻያ ተደርጎባቸው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በቃለ መጠይቁ ላይም አስር ክፍት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን አምስቱም መምህራን  እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን አስተያየት በተገቢው መንገድ

## 3.5. የመረጃ አጠነቃቀርና አተናተን ስልት

የዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ምንጭ" መጽሀፍ ግምገማ" መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የሰነድ ፍተሻው ዋና አላማም ለጥናቱ በተመረጠው የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀትና አቀራረብን በጥልቀት መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ በመዛግብት ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በዓይነት በዓይነት ተደራጅተው እንዲቀርቡ ሆኗል፡፡ በመጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችና ይዘቶች አቀራረብ Grellet (1991)፣ እና Celece-Muricia(1991) ጸሀፍት ባስቀመጧቸው መስፈርቶች አማካኝነት የይዘቶችንና የመልመጃዎችን አቀራረብ መሰረት በማድረግ ተደራጅተው ተንትነዋል፡፡

የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን ገላጭ የመረጃ መተንተኛ ስልት በተግባር ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ በመዛግብት ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች ከአጥኝዋ እይታ አንጻር በገላጭ የአተናተን ስልት ከተተነተኑ በኋላ የቃለ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን እይታ አንጻር የተገኙት መረጃዎች የቁጥር መለኪያ ተሰጥቷቸው በመጠን በመቶኛ ተገልጽዋል

የክፍል ውስጥ አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በገላጭ የአተናተን ስልት የቀረቡ ሲሆን በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአጥኝዋ እይታ አንጻር የቁጥር መለኪያ ተሰጥቷቸው በመቶኛ ከተተነተኑ በኋላ በገላጭ የአተናተን ስልት ተገልጸዋል፡፡

የትንተናው ትኩረት በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች እና የይዘቶች አቀራረብ ላይ ነው፡፡ ይኸውም ትኩረት ያደረገው ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ ደረጃ ተስማሚ ናቸው? የመልመጃዎቹ አዘገጃጀት የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን አካተዋል? የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ለማቅረብ አጋዥ ናቸው? የሚሉት ነገሮች በዋናነት ትኩረት የተደረገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመረጃ ትንተና

ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2007 ዓ.ም በተዘጋጀው የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብና አዘገጃጀት መፈተሽ ነው፡፡

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለጸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በዋናነት ሰነድ ፍተሻ  ሲሆን በአጋዥነት ቃለ መጠይቅ ነው፡፡

የዚህ ክፍል አላማም የተሰበሰቡትን መረጃዎች መተንተን ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ለመምህራን የቀረቡ ቃለመጠይቆች በሰነድ ፍተሻው ወቅትም አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን መምህራንን በሚመለከት በዋናነት ከመምህራኑ የቃል መጠይቅ የተገኙት መረጃዎችም አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብና አዘገጃጀት  አስመልክቶ የተገኙ መረጃዎች ከመተንተናቸው በፊት ስለ መማሪያ መጽሐፉ ጥቂት መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1. የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ዳራ

የአምስተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተስማምቶ የቀረበ ሲሆን መጽሐፉ የታተመው በ2007 ዓ.ም ሲሆን አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ2009 ዓ.ም ነው፡፡ መጽሐፉ ወደ ዋናው የትምህርት ክፍሎች ከመግባቱ በፊት በመግቢያው ላይ የስርዓተ ትምህርቱን መሰረታዊ መርሆዎች፤ ከትምህርት ቤት ውጭ የተማሪዎችንና የወላጆችን ትምህርታዊ ተግባራት እንዲሁም የመጽሐፉን የይዘት አደረጃጀት በማስተዋወቅ ይጀምራል፡፡ ዋናውን የመጽሐፉን ትምህርታዊ አቀራረብ ስንቃኝ ደግሞ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ በሶስት ሳምንት፣ አንዱ ሳምንት ደግሞ በሶስት ቀናት ተከፋፍሎ  እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ መጽሐፉ በአመት ውስጥ በሰላሳ ሳምንት ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን የመጽሐፉ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲታይ ሰባት ዋና ዋና የቋንቋ ይዘቶች አካቶ ይዟል፡፡ እነሱም፡- የቃላት ጥናት፣ አንብቦ መረዳት፣ የቃላት እውቀት፣ መጻፍ፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ ቃላዊ ክሂሎች (መናገርና ማዳመጥ) እና ሰዋስው ናቸው፡፡ ሌላው መጽሀፉ በመጨረሻ ገጾች ላይ

የተለያዩ የቃላትን ፍች የሚያሳዩ ሙዳዬ ቃላትና ዋቢ መጻህፍትን ይዟል፡፡ በአጠቃላይ መጽሀፉ 233 ገጾች አሉት፡፡

### 4.1.2. የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መረጃ

**ሰንጠረዥ ፡-1. ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን አጠቃላይ መረጃ**

| በዋናነት የሰለጠኑበት መስክ | ፆታ | ዕድሜ | የአግልግሎት ዘመን በአመታት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በሰርተፍኬት | በዲፕሎማ | በድግሪ |
| አማርኛ | ሴ | 38 | - | 8 | |
| አማርኛ | ሴ | 43 | - | 14 | 7 |
| አማርኛ | ወ | 37 | - | 7 | 5 |
| አማርኛ | ሴ | 47 | 9 | 10 | 4 |
| አማርኛ | ሴ | 32 | - | 7 | 2 |

ከሰንጠረዥ አንድ እንደምንረዳው ተተኳሪ መምህራኑ በዋናነት የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ነው፡፡ የትምህርት ደረጃቸውን በተመለከተም አራቱ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን አንዲት መምህርት ዲፕሎማ እንዳላት ታውቋል፡፡ የመምህራኑ የአገልግሎት ዘመንም ከ 8 እስከ 23 አመታት ባለው ውስጥ ያገለገሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቋንቋን በማስተማር ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ በመሆናቸው የሚሰጡት መረጃ ለጥናቱ ተገቢና ተዓማኒ እንዲሆን ይረዳል ተብሎ ይገመታል፡፡

### 4.1.3. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የንባብ ክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ

በ2007 ዓ.ም የተዘጋጀው የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በአስር ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፤ በውስጡም ሰላሳ ምንባቦችን አካቶ ይዟል፡፡ በሁሉም ምዕራፎች ስር የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ ለዚህ የመረጃ ትንተና እንዲያመች አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና በሚል ንዑስ ርዕስ ለይቶ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

### 4.1.4. አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና

የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረ-ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን የሚገልጹ ሲሆን በእነዚህ

አቀራረብ ማስተማር ደግሞ የተሻለ ውጤታማ መሆኑን Lindsay and Knight (2006) ገልጸዋል፡፡

**ቅድመ ንባብ**

ቅድመ ንባብ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም ምላሽ የሚሰጡበት ሂደት ነው፡፡

የዚህ መጽሐፍ አቀራረብም ሲታይ በአብዛኛዎቹ ምንባቦች ውስጥ ሁሉም ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች አሏቸው፡፡ በቅድመ ንባብ ጊዜ መካሄድ ያለባቸው ክንዋኔዎች የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነቃቃት፣ ቀደምት እውቀታቸውን በመጠቀም የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲገምቱ ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም በ2007 ዓ.ም በታተመው የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሁሉም ምንባቦች በፊት መቅረባቸው ብቻ ሳይሆን የማንበብ ፍላጎት በማነቃቃት የምንባቦቹን ፍሬ ሀሳቦች እንዲገምቱ የሚያስችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች አቀራረብ ማሳያ እንዲሆኑ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አምስት- ገጽ 81 ላይ "ፅዳትና ንጽህና" በሚል ርዕስ ስር ላይ “አከባቢያችሁ ቆሻሻ እንዴት ይወገዳል? እንዲሁም ገጽ 104 ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ከእንስሳትና ከዕጽዋት የሚገኙ ምግቦችን ዘርዝሩ?" እነዚህና ሌሎች መሰል ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ባህርይ የተማሪዎችን ቀደምት ልምድ የሚመለከት፤ ቀጥሎ ወደሚማሩት ትምህርት የሚያመላክቱ፣ የተማሪዎችን የመማር ሂደት በቅድሚያ የሚያመቻቹ ናቸው፡፡

እነዚህ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ቀደምት እውቀት ከጽሁፎች ይዘቶች ጋር በማያያዝና በማነቃቃት የምንባቦቹን ፍሬ ሀሳቦች እንዲገምቱ የሚያስችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ጥያቄዎቹም ምንባቦቹ የሚመልሷቸው በመሆናቸው ተማሪዎች ቀደምት እውቀታቸውን ከምንባቡ ሀሳብ ጋር እንዲያ ዛምዱ ጽሁፉን እንዲገምቱ የሚረዱ ናቸው፡፡

**የንባብ ጊዜ ተግባራት**

የንባብ ጊዜ ተግባራት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በንቃት አየተከታተሉ መሆናቸውን የሚቆጣጠሩበት ጊዜ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን  የንባብ ጊዜ ተግባራት እንመለከታለን። የንባብ ጊዜ ተግባራት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በንቃት ላይ የተመሰረተ ንባብ እያካሄዱ መሆናቸውን የሚቆጣጠሩበትና ተማሪዎቹ የበለጠ ለንባብ እንዲነሳሱ የሚያግዙ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው። ስለዚህ በተተኳሪው  ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የንባብ ጊዜ ተግባራት አቀራረብን አስመልክቶ ምሳሌዎችን እንመልከት።

"ሐዋና ጓደኞቿ"   በሚል ርዕስ የቀረበውን በትረካ የቀረበ ምንባብ ግምታችሁን እያረጋገጣችሁ ድምጽ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ። (ገጽ22) "የአየርና የውሃ ብክለት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ የምክንያትና የውጤት ትስስርን በማስተዋል አንብቡ። (ገጽ 55)"ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ መረዳታችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ። በምታነቡበት ጊዜ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማችሁ መዝግቡ የሚሉና ሌሎችንም ትዕዛዛት የያዙ ክንውኖች ቀርበዋል።

እነዚህን የንባብ ጊዜ ተግባራት አቀራረብ ተማሪዎቹ እያነበቡ እያሉ ወደፊት የሚሆነውን በመተንበይ እንዲያነቡና በየአንቀጹ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን እንዲጽፉ የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህም አቀራረቦች ተማሪዎቹ የበለጠ ለምንባቡ እንዲነሳሱ እገዛ ያደርጋሉ።

**አንብቦ መረዳት(ድህረ ንባብ)**

አንብቦ መረዳት (ድህረ ንባብ) የግምገማ ጥያቄዎች ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ ምንባቡን አንብቦ መስራት ላይ ያተኮረ ነው።

ድህረ ንባብ (አንብቦ መረዳት) ተግባራት በአብዛኛው የግምገማ ስራዎችን የሚይዝ ሲሆን የተነበበውን ምንባብ መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጭ ካለው አለም ጋር በማዛመድ ሃሳብ እንዲያቀርቡባቸው የሚያስችሏቸው ጥያቄዎች የሚካተቱበት ነው። አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች የምንባቡን ዓላማ፣ የጸሀፊውን አመለካከት፣ የአንባቢውን አረዳድና ሌሎችንም ነጥቦች የሚዳስሱ በመሆናቸው በተለያየ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ። ይኸውም በክፍት ጥያቄዎች፣ በምርጫ ሰጪ፣ በእውነት /ሀሰት፣ በአዛምድ እና በሌሎችም የአቀራረብ ስልት እንደ ምንባቡ ባህሪ ጥያቄዎቹ ተለዋዋጭነት ሊኖራቸው ይችላል። በመሆኑም በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የጥያቄዎቹ አቀራረብ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል ።

**ሰንጠረዥ ፡-2. በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባህርይ**

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው በአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ

| ምዕራፍና ርዕስ | የመልመጃ ጥያቄ አይነቶች | | | | በየምዕራፉ ያሉ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክፍት ጥያቄዎች | ዝግ ጥያቄዎች | | | |
| | | እውነት/ሀሰት | አዛምድ | ምርጫ | |
| ምዕራፍ አንድ ጓደኝነት | 23 | - | 6 | - | 29 |
| ምዕራፍ ሁለት አከባቢያችን | 14 | 3 | - | 6 | 23 |
| ምዕራፍ ሶስት ልማዶች | 22 | 6 | - | - | 28 |
| ምዕራፍ አራት የትራፊክ ደህንነት | 20 | - | - | 5 | 25 |
| ምዕራፍ አምስት ጽዳትና ንጽህና | 18 | - | - | 7 | 25 |
| ምዕራፍ ስድስት ምግብ | 23 | - | 8 | - | 31 |
| ምዕራፍ ሰባት የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ | 16 | - | - | 8 | 24 |
| ምዕራፍ ስምንት ባህላዊ ጨዋታዎች | 33 | - | - | 4 | 37 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ ሥነ-ቃል | 14 | | | 6 | 20 |
| ምዕራፍ አስር ኤች አይ ቪ. ኤድስ፤ መድሎና መገለል | 22 | 4 | | 6 | 32 |
| ድምር | 205 | 13 | 14 | 42 | 272 |
| በፐርሰንት | 74.81 | 4.74 | 5.1 | 15.32 | 100 |

አስር ምዕራፎች ቀርበዋል፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች በተካተቱ ምንባቦች ውስጥ 272 አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችም በክፍት 205(74.81%) ዝግ 67 (25.18%) ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዝግ የቀረቡት ጥያቄዎች በእውነት ሀሰት፣በአዛምድና በምርጫ የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ከፍተኛው የአንብቦ መረዳት ጥያቄ በክፍት መልክ መቅረቡን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡

ይህም አቀራረብ ክፍት ጥያቄዎች መላሹ ነጻ ሆኖ ያለ ገደብ የራሱን ሀሳብ በተረዳው መንገድ የሚገልጽባቸው የጥያቄ አይነቶች በመሆናቸው የአንባቢውን የመተንበይ፣ የመገመት፣ የማብራራትና የማጠቃለል ችሎታዎችን ለማዳበር ከዝግ ጥያቄዎች የተሻሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም በተተኳሪው ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎችም ሀሳባቸውን በነጻነት ለመግለጽ አመችነታቸው ከፍ ያለ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አቀራረብን ማሳያ እንዲሆኑ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ገጽ 21 ላይ "አከባቢያችን" በሚል ርዕስ ባለው የምንባብ ጭብጥ ስር ፊደል ተራ ሀ. የአየርና የውሀ ብክለት መንስኤዎችንና የሚያደርሱትን ጉዳት አሳጥራችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ገጽ 57. ፊደል ተራ ለ. ያለ ዕድሜ ጋብቻ የሚፈፀምበት ዋነኛ ምክንያት ምንድ ነው? እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

የእነዚህ ጥያቄዎች አቀራረብ የምንባቡን ዋና ሀሳብ ወይም ጭብጥ መሰረት በማድረግ በራስ አገላለጽ እንዲጽፉ የሚረዳ ነው፡፡ ይህም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማዳበር ያግዛል፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ 184 ተግባር 3 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባብ መሰረት መልሱ፡፡

"ነጭ አሞራ በሮ ይገባል ዋሻ፤

ያገርህን ጠላት አሳጣው መድረሻ" የሚለው ግጥም መልዕክት ምን ይመስላችዋል?

1. ቃላዊ ግጥሞች ባይኖሩ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ምን የሚያጎድሉት ነገር ያለ ይመስላችኋል?

ይህ የጥያቄ አቀራረብ መተርጎምና ማብራራትን መሰረት በማድረግ የቀረበ ነው፡፡ እነዚህ ብልሀቶች ተማሪዎች ስላነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚያስችሉ በመሆናቸው አንብቦ የመረዳትንና የተለያዩ የቋንቋ ችሎታን ለማዳበር ያግዛሉ፡፡

ምዕራፍ ሰባት- ገጽ 133 ተግባር 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ ጻፉ፡፡
ሀ.ከአጋዘን አስተኔዎች በቡድን የማይታዩ የትኞቹ ናቸው?
ለ. ከአጋዘን አስተኔዎች ውስጥ በመንጋቸው ውስጥ ብዛት ያላቸው የትኞቹ ናቸው?
እነዚህ ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ሆነው ምላሻቸውም መመራመር የሚያስፈልጋቸውና የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ሲሆኑ በራስ አገላለጽ ሀሳብን በጽሑፍ ለመግለጽ የሚያግዙ ናቸው፡፡ ይህም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያግዛሉ፡፡
ቀጥሎ ደግሞ ለመምህራን የቀረበውን የቃለ መጠይቅ ምላሽ መሰረት በማድረግ ትንታኔ ይሰጣል፡፡ ለመምህራን የተዘጋጁት የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ፡-3. ለአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን አላማ የማሳካት ብቃታቸው.**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች |
|---|---|
| 1 | በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ |
| 2 | ይዘቶቹ የአንብቦ መረዳትንና የተለያዩ የቋንቋ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶችን አሟልቶ የመያዝ ሁኔታ |
| 3 | መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ<br>ለክሂል መልመጃዎች ግልጽ የሆኑ መመሪያዎች የመቅረብ ሁኔታዎች |
| 4 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ ለማድረግ ያላቸው አቅም |
| 5 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የማንበብ ክህሎት ለማዳበር ያላቸው እገዛ |
| 6 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት |
| 7 | በየክፍለ ጊዜው የተሸነሸነው ይዘት ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣመ መሆኑ |
| 8 | በመጽሐፉ ውስጥ በየምዕራፉ የቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ጥያቄዎች ተካተው መገኘታቸው |
| 9 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ይዘት ከንባብ ክህል ጋር ያለው ትስስር |
| 10 | የክሂል መልመጃዎቹ ተማሪዎች በውይይት እንዲሰሩ የሚጋብዝ መሆኑ |

ከላይ በሰንጠረዥ የቀረቡት የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ለአምስቱ አምስተኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ሲሆን እያንዳንዳቸው መምህራን የየራሳቸውን መልስ በመጠይቁ መሰረት ሰንዝረዋል፡፡ በመሆኑም መምህራን የመለሱት ምላሽ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመጠይቅ አንድ ላይ የቀረበውን ምላሽ መምህርት አንድና መምህርት ሁለት በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ እገዛ አላቸው፡፡ ነገር ግን መጽሐፉን እያስተማርንበት ወይም እየተገለገልንበት እንደ መሆኑ መጠን አልፎ አልፎ አንዳንድ ይዘቶች ከክፍለ ጊዜው ጋር የማይጣጣም መሆኑን አስተውለናል በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም መምህር/ት/ ሶስት፣አራትና አምስት በበኩላቸው በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ ከፍተኛ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

መጠይቅ ሁለትን በተመለከተ በተተኳሪው ክፍል ላይ የተካተቱ የመልመጃዎቹ ይዘት የአንብቦ መረዳትንና የተለያዩ የቋንቋ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶችን አሟልቶ የመያዝ ሁኔታቸው ከፍተኛ መሆኑ በአምስቱም መምህራን ሊገለጽ ችሏል፡፡

በመጠይቅ ሶስት የተሰጠውን ምላሽ ለማስቀመጥ ስንሞክር በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለክሂል መልመጃዎች ግልጽ የሆኑ መመሪያዎች የመቅረብ ሁኔታቸው የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላሽ አብዛኛዎቹ በተተኳሪው መጽሐፍ ላይ የቀረቡት የመልመጃ ጥያቄዎች ግልጽ በሆኑ መመሪያዎች የተገለጹ ሲሆን በተወሰነ መልኩ ደግሞ ግልጽነት የጎደላቸውና ተማሪዎቹ እንዴት መስራት እንዳለባቸው የማይጠቁሙ መልመጃዎችን ለማስተዋል ችለናል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በመጠይቅ አራት የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ ለማድረግ ያላቸው አቅም የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላሽ በብዛት ቋንቋውን እንዲካኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ የመልመጃዎቹን ጥያቄ ለመስራት ሲሉ በተደጋጋሚ ምንባቡን ማንበባቸው አይቀሬ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ምንባቡን አነበቡት ማለት ደግሞ ቋንቋውን በሚገባ እየተረዱት ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ቋንቋውን እንዲካኑ ያደርጋቸዋል የሚል ምላሽ ለመስጠት ሞክረዋል፡፡

በመጠይቅ አምስት የተሰጠውን ምላሽ ደግሞ ስንመለከት መምህራን የሰጡት ምላሽ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የማንበብ ክህሎት ለማዳበር ከፍተኛ እገዛ አላቸው፡፡ ምክንያቱም በጥያቄ ቁጥር አራት ላይ ለመመለስ እንደሞከርነው ተማሪዎች መልመጃዎችን ለመስራት ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ደጋግመው የማንበብ ልምድን ስለ ሚያካብቱ ከፍተኛ እገዛ አላቸው በማለት ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

በመጠይቅ ስድስት ላይ መምህራን የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት ከፍተኛ ቢሆንም አንዳንድ ይዘቶች ላይ ከተማሪዎች አቅም በላይ የሆኑ የቃላት ክብደትና የይዘት ስፋት አስተውለናል ይህ መሆኑ ደግሞ ተማሪዎቹ የዕድሜ ደረጃቸው ዝቅተኛ እንደመሆኑ መጠን እውቀታቸው የተገደበ እንዲሆን ያደርጋቸዋል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በመጠይቅ ሰባት ላይ የቀረቡ ምላሾች ደግሞ ሁለት መምህራን ለክፍለ ጊዜው የተሸነሸነው ይዘት ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር በአብዛኛው የተጣጣመ ነው ሲሉ የተቀሩት ሶስት መምህራን ደግሞ ተማሪዎቹ ህጻናት እንደመሆናቸው መጠን ከዕድሜያቸው ጋር የተጣጣመ ይዘትና የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ሊሆን ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በተተኳሪው መጽሐፍ ላይ እንዳየነው በአብዛኛው የተመጣጠነ የጊዜ ርዝማኔ እንዳልሆነ አስተውለናል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ተማሪው ሳልጨርስ ሰዓቱ አለቀ አላለቀ ብሎ ሲጨነቅ ማወቅ የሚገባውን ነገር ሳያውቅ እንዲሄድ ያደርገዋል በማለት ምላሻቸውን አስቀምጠዋል፡፡

በመጠይቅ ስምንት ላይ የቀረበውን ጥያቄ አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላሽ በሁሉም ምዕራፎች ላይ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ተግባራት ተካተው እንደተገኙ በምላሻቸው አረጋግጠዋል፡፡

በመጠይቅ ዘጠኝ ላይ የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ይዘት ከንባብ ክሂል ጋር ከፍተኛ የሆነ ትስስር እንዳላቸው ለማስተዋል እንደቻሉ ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

መጠይቅ አስር አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላሽ የቀረቡት የክሂል መልመጃዎች ከሞላጎደል ተማሪዎቹ በውይይት እንዲሰሩ የሚጋብዙ ናቸው በማለት ምላሻቸውን አስቀምጠዋል፡፡

ለቃለ መጠይቅ የቀረቡት አምስቱ መምህራን የሰጡትን ምላሽ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀመጥ በቃለ መጠይቁ የተገኘው ውጤትን ስንመለከት የተሸነሸነው ይዘት ከተሰጠው የጊዜ

ርዝማኔ ጋር የተጣጣመ አለመሆኑን፣ በአብዛኛው የመልመጃው ይዘት ግልጽ በሆነ መመሪያ የቀረበ መሆኑን፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ እገዛ እንዳላቸው፣ የተለያዩ የቋንቋ ክሂልን በቅንጅት እንደ ሚያስተምሩ፣ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ የሚያደርግ መሆኑ፣የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ የሚያደብሩ፣ ከሞላ ጎደል ለክፍል ደረጃቸው የማይመጥኑ ይዘቶች እንዳሉ፣ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ተግባራትን አካቶ የያዘ መሆኑን፣ከንባብ ክሂል ጋር ከፍተኛ ትስስር እንዳለውና ከሞላ ጎደል በውይይት እንዲሰሩ የሚጋብዝ መሆኑ መምህራን ለቃለ መጠይቁ በሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻውና  ከቃለ-መጠይቁ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በመጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ አቀራረብ ከምንባቡ በፊት ስለምንባቦቹ ይዘት የመገመት የቅድመ ንባብ ተግባራት፣ በምንባቡ ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በማካተት ከምንባቡ ይዘት በመነሳት እንዲጽፉ የሚያግዙ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ እነዚህም የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስ እንዲገምቱ የሚያደርጉ እንዲሁም ምንባቡን መሰረት በማድረግ በራሳቸው አገላለጽ እንዲያብራሩና የምንባቡን ጭብጥ አሳጥረው እንዲጽፉ የሚያግዙ ናቸው፡፡ ይህም አንብቦ የመረዳትንና  የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ እንዲተገበሩ የቀረቡት የመልመጃ ጥያቄዎች ክሂሎቹን ለማዳበር በሚያስችል መልኩ የቀረቡ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ይዘት ለልምምድ በሚቀርብበት ጊዜ በቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው የትምህርቱ ዓላማ ነው፡፡ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ የመለማመጃ ጥያቄዎች ግልጽ በሆኑ መመሪያዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች  መመሪያ አቀራረብ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡

**ሰንጠረዥ፡-4. በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች መመሪያ አቀራረብ**

| ተ.ቁ | የመልመጃ ጥያቄዎቹ የሚመለሱበት መንገድ | ጠቅላላ ብዛት በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | በቃል እንዲመለሱ የቀረቡ | 11 | 20.75 |
| 2 | በጽሁፍ እንዲመለሱ የቀረቡ | 34 | 64.15 |
| 3 | በምን ሁኔታ እንደሚመለሱ ያልተገለጹ | 8 | 15.09 |
|  | ጠቅላላ ድምር | 53 | 100 |

በሰንጠረዥ 4 ላይ እንደምንረዳው በመጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ውስጥ 11(20.75%) በቃል እንዲመለሱ፣ 34(64.15%) በጽሁፍ እንዲመለሱ፣ 8(15.09%) ደግሞ በቃል ይሁን በጽሁፍ በግልጽ ትዕዛዝ የሌላቸው መልስ እንዲሰጥባቸው ብቻ የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች መመሪያ አቀራረብ አብዛኛዎቹ በጥንካሬያቸው የሚገለጹ ናቸው።

በአንጻሩ ደግሞ ለልምምድ እንዲሆኑ ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል ግልጽነት የሌላቸውና ተማሪዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገብሩት ግልጽ ያልሆኑ መመሪያዎች እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል። የእነዚህ መመሪያዎች ችግርም ተማሪዎች ተግባራቱን በምን መልኩ እንደሚተገብሯቸው ግልጽነት የሌላቸው ናቸው። ይህም ሲባል አተገባበራቸው በቃል ይሁን በጽሁፍ፣ በተናጠል ይሁን በጥንድ፣ በግል ይሁን በቡድን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ግልጽ በሆነ መልኩ አለመገለጻቸው ነው።

በአጠቃላይ በመጽሀፉ ውስጥ ለክሂል መልመጃዎቹ የቀረቡትን መመሪያዎች በመመርመር የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ጥሩ የሚባሉ መመሪያዎች መኖራቸውን ነው። ይሁን እንጂ ግልጽነት የሌላቸው ከተማሪዎች የሚጠበቀው ተግባር እንዴት እንደሚያከናውኑት በትክክል የማይገልጹ መመሪያዎችም እንዳሉ የመረጃ ትንተናው ያመለክታል። ከቃለ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል

### 4.1.5. የአንብቦ መረዳት ትምህርት የይዘቶች አቀራረብ ትንተና

ለአንድ የክፍል ደረጃ የሚቀርብ የትምህርት ይዘት የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዳራዊ ጉዳዮችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል። አለበለዚያ በመማር ማስተማሩ ሂደት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። በመሆኑም የመማሪያ መጽሀፉ ይዘቶች አቀራረብ ለአብነት ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል።" ምዕራፍ ሶስት "ቡና ጠጡ" በሚለው ምንባብ ስር ገጽ 43 ፊደል ተራ ሀ."ጎረቤቶቹ ቡናው ከመፈላቱ በፊት የመጡት ለምንድን ነው? ምዕራፍ አራት ገጽ 61 ከቤታችሁ ወደ ትምህርት ቤታችሁ ስትሄዱ ወይም መንገድ ስታቋርጡ ምን ዓይነት ጥንቃቄዎችን ታደርጋላችሁ?

ምዕራፍ ዘጠኝ "ሥነ-ቃል" ገጽ 181 ተግባር 1

1. በአካባቢያችሁ ሰዎች በሥራ፣ በሠርግ ወ.ዘ.ተ ጊዜ የሚያዜሚቸውን ግጥሞች አስታውሳችሁ የምታውቋቸውንና በግጥም የሚቀርቡ የልጆች ጨዋታዎችን ስማቸውን ተናገሩ።

እነዚህ ይዘቶችም በአብዛኛው ከላይ ለተዘረዘሩት መሰረታዊ ነገሮች ትኩረት ተሰጥቷቸው የተዘጋጁ እንደሆኑ ያሳያል። ምክንያቱም በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ አንብቦ የመረዳት ይዘቶች በደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገቡ፣ አብዛኛዎቹ ከተማሪዎች አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችና መልመጃዎች የተካተቱ መሆናቸው ነው። ለዚህም ማሳያው በአስሩም ምዕራፎች ስር የቀረቡት ምንባቦች ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸውና የአንብቦ መረዳት ተግባራትም ምንባቦቹን መሰረት አድርገው በመዘጋጀታቸው ነው።

### 4.1.6. መምህራን ስለ አንብቦ መረዳት መልመጃ አዘገጃጀትና አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ

አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ከምንባብ ቀጥሎ የሚመጡ በተነበበው ጽሁፍ ላይ መሰረት ያደረጉ እንደሆኑ Nuttal (1988) ገልጸዋል። እንደ ምሁራኑ ገለጻ ቋንቋን ለማስተማር ዓላማ ባደረገ የንባብ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መመለስ እንዲያስችላቸው መምህራን በቅድመ ንባብ ተግባራት ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲፈትሹ ያደርጋሉ። የሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትም ይህን የተከተሉ ናቸው።

### 4.1.7 የመምህራኑ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም በቅድመ ንባብ ተግባር የተፈተሹ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት፣ በንባብ ጊዜ የሚያዙ አጫጭር ማስታወሻዎችን ከንባብ በኋላ የሚካሄዱ ውይይቶችን፣ የጽሁፍ ተግባራትና ሌሎች ክሂሎችን አጠቃለው የሚይዙ ናቸው። ይህም ተማሪዎች መሰረታዊ የሆኑ በይዘት ላይ ያተኮሩ መልመጃዎችን እንዴት እንደሚሰሩ በመጠቆም ልምድን ያዳብርላቸዋል። በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አንባቢ የአንድን ጽሁፍ አጠቃላይ መልዕክት ከተለያዩ አተያዮች አንጻር መገንዘብን ለመመርመር የሚዘጋጁና ክሂልን ለማዳበር የሚረዳ መንገድን የሚያሳዩ ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ በርካታ ነጥቦች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የአንባቢያንን ችሎታ በመመዘን ላይ ብቻ ያተኮሩ ሳይሆኑ አንባቢያኑ አንድን ጽሁፍ ለመረዳት በራሳቸው የሚፈጥሩትን አዳዲስ ስልት እንዲቀይሱየሚገፋፉ መሆን እንደሚኖርባቸው የተለያዩ ምሁራን

አብራርተዋል፡፡ ምሁራኖቹ እንደገለጹት ምንባብን መሰረት ያደረጉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተከታታይነት ያላቸው የመረዳትን ሁኔታ ማረጋገጫ መልመጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መልመጃዎች ደግሞ እንደ ጽሁፉ ባህሪ ተለዋዋጭነት ያላቸው ይሆናሉ፡፡

ከመጠይቁ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ማንበብና መጻፍ ጥብቅ የሆነ ትስስር ስላላቸው አንብበው ከተረዱት ነገር ተነስተው እንዲጽፉ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ጠቀሜታውም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የመጻፍ ክሂላቸውን ለማሳደግ እንደሚረዳቸው ነው፡፡ ይህም የሚያሳየን አብዛኛዎቹ መምህራን ስለ ቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ግንዛቤው ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

**በአጠቃላይ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ መምህራን ስለቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ** አቀራረብ ግንዛቤው ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለጸው ይህ ጥናት የተካሄደው ለሦስት ጥያቄዎች መልስ በመስጠት የጥናቱን አላማዎች ለማሳካት ነው፡፡ በተደረገው ጥናትም ጥያቄዎቹ መልስ ስላገኙ አላማዎቹ ተሳክተዋል፡፡ የጥያቄዎቹ መልስ የተገኘው ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ ውጤት ትንተና ሲሆን ትንተናውን መሰረት ያደረገው የውጤት ማብራሪያ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ጥያቄዎች ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚገባቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ሲሆኑ ጥያቄዎቹም በ2007 ዓ.ም በታተመው የአምስተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ መረዳት መልመጃዎች ሦስቱን የንባብ ትምህርት ትግበራ ደረጃዎች ያካተቱ ናቸውን? የተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ግልጽ ከሆኑ መመሪያ ጋር ቀርበዋልን? የተተኳሪው ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ያዳብራሉን? የሚሉት ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘትም በዋናነት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብን መሰረት ያደረገ የሰነድ ፍተሻ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም አስር ለቃለ መጠይቅ የሚሆኑ መጠይቆችን በማዘጋጀት ለአምስት መምህራን ቃለ መጠይቁ ቀርቦላቸው መረጃ ተሰብስቧል፡፡መረጃውን መሰረት በማድረግ ውጤት ትንተናም ተከናውኗል፡፡

የውጤት ትንተናውም የአንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብና አዘገጃጀት ዙሪያ የተለያዩ ውጤቶች መገኘታቸውን ያመለክታል፡፡

በመጀመሪያ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን አንብቦ መረዳት ይዘቶችና መልመጃዎች አዘገጃጀት ስንመለከት ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አብዛኛዎቹ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች በደረጃው የሚገኙ ተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገቡ፣አብዛኛዎቹ ከተማሪዎች አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችና መልመጃዎች የተካተቱ መሆናቸውን የትንተናው ውጤት ያመለክታል። መማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ ማሟላት ካለባቸው ባህሪያት መካከል የይዘት ተገቢነት ሲሆን በደረጃው የሚገኙ ተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገቡ፣ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችና መልመጃዎች መሆን እንዳለባቸው ተገልጿል። በመሆኑም የጥናቱ ውጤት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል።የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ በርካታ ነጥቦች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱትን Grellet (1991:6-9) ገልጸዋል። እነሱም፡- ከአጠቃላይ ጭብጥ መጀመር፣ የጥያቄዎችን ስብጥር መጠበቅ፣ ከልዩልዩ ክሂሎች ጋር ማቀናጀትና በመልመጃ ጥያቄዎችና በፈተና ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ናቸው

ሁለተኛው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ የተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ግልጽ ከሆኑ መመሪያ ጋር እንዴት ቀርበዋል? የሚለው ሲሆን ተማሪዎች የማንበብ ክሂሎችን ሲለማመዱ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲተነብዩ፣ ትርጉም እንዲሰጡ፣ ሳነበቡት ወይም ለጻፉት ነገር ማጠቃለያ እንዲሰጡ ሆነው ሲዘጋጁ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እንደ መሰረታዊ አንብቦ መረዳት ማጎልበቻ ብልሃት ተደርጎ ይወሰዳል ። በመሆኑም የአምስተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብን በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አንብቦ የመረዳት ተግባራት ከተለያዩ የቋንቋ ክሂል ጋር ትኩረት ተሰጥቷቸው በቅንጅት እንደቀረቡ የተገኘው መረጃ ትንታኔ ያመለክታል። በመሆኑም የጥናቱ ውጤት ንድፈ ሀሳቡን ካቀረቡት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር በአብዛኛው የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል።

ሶስተኛው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ የተተኳሪው ክፍል የአማርኛ ተተኳሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ያዳብራሉን? የሚለው ሲሆን የጥናቱ ውጤት ተስፋዬ (1995) ካቀረቡት ንድፈ ሀሳብ ጋር በአብዛኛው የሚደጋገፍ ነው።

የንባብን ክሂል ለማዳበር የምንመርጠው የጽሑፍ መጠን ክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ አንፃር የተጣጣመ መሆን አለበት። ምክንያቱም ጽሁፍን ለማንበብ የሚወስድብን ጊዜ እና ከንባብ በኋላ ለሚሰሩ ተግባራት የምንሰጠው ጊዜ ከአለን አጠቃላይ ጊዜ ጋር ካልተጣጣመ ልናዳብረው የፈለግነውን የንባብ ክሂል ውጤታማ ልናደርገው አንችልም Lindsay and Knight (2006)። ይሁን እንጂ በንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የቀረቡት ተግባራትና የተሰጠው ጊዜ ተመጣጣኝ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በመሆኑም የጥናቱ ውጤት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር በከፊል ተቃርኖ አለው። Durkin (1977:399) እና Grellet (1991:8) እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳት የምንባብን ሃሳብ የመገንዘብ፣ የማብራራት፣ የመከለስ ፅንሰ ሃሳቦችን የማዛመድ፣አንድነትና ልዩነቶችን የመመርመር፣ የመከራከርና የመወያየት ችሎታዎች ማንጸባረቂያም በመሆኑ ከመጻፍ፣ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች ጋር ተነጣጥሎ ሊታይ አይችልም።ይህም ሲባል ለንባብ የቀረበ ጽሑፍን በሚገባ ካነበቡ በኋላ በጽሁፉ ሀሳብ ዙሪያ መከራከርና መወያየት ከንግግር፣የጽሁፉን ሀሳብ መከለስና ማስታወሻ መያዝ ከጽሑፍ እንዲሁም ጽሑፉን ከሚደመጥ ነገር ጋር ከዜናና ከሌሎች ዘገባዎች መለየት ከማዳመጥ ክሂል ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ያደርገዋል።

የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንዲሆን የመስኩ ምሁራን የሚገልጹ ሲሆን በእነዚህ አቀራረብ ማስተማር ደግሞ የተሻለ ውጤታማ መሆኑን Lindsay and Knight (2006:74-81) ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የውጤት ትንተና ማብራሪያው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረባቸው ምን እንደመሚመስልና በአቀራረባቸው ውስጥ ያለውን ጥንካሬና ክፍተት በመተንተን ይዘቶቹ ማሟላት ያለባቸውን ነገሮች ምን እንደሚመስል በመተንተን ተብራርተዋል። የውጤት ማብራሪያውም በምዕራፍ ሁለት የተገለጹትን የምሁራን ንድፈ ሃሳቦች መሰረት ያደረገ ነው።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2007ዓ.ም በተዘጋጀው የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብንና አተገባበር በመገምገም ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን በመለየት ማሳየት ነው። ጥናቱ ያነሳቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ ለጥናቱ አላማ ግብ መምታት አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተግባር ላይ ውለዋል። እነዚህም የመዛግብት ምርመራና የቃል መጠይቅ ናቸው። የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የሚከተሉት የማጠቃለያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል።

# 5.ማጠቃለያ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

ከዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች መካከል የመጀመሪያው በ2007 ዓ.ም ለአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ሶስቱ ትግበራ ደረጃዎችን አካቶ የያዘ መሆን አለመሆኑን መመርመር ሲሆን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ችሎታና ዳራዊ እውቀታቸውን ከግንዛቤ ባስገባ ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይዘቶቹ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረባቸውን የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማ በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ግልጽ ከሆነ መመሪያ ጋር የቀረቡ መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ መልመጃዎች ግልጽ ከሆነ መመሪያ ጋር የቀረቡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ መልመጃዎች ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል የመለማመጃ ጥያቄዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገበሩ የተሟላ መረጃ የሚሰጡ የተካተቱ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ስለ መልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚገኙ የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

ሶስተኛው የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማ በተተኳሪው ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ማዳበር አለማዳበራቸውን መፈተሽ ሲሆን እንደሚያዳብሩ መፈተሽ ሲሆን አብዛኛዎቹ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማዳበር አመቺ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ በንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ ለማስተማሪያነት የቀረቡት ይዘትና የተሰጠው ጊዜ ተመጣጣኝ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የተዘጋጁት መልመጃዎች ከመመሪያ ግልጽነት አንጻር አብዛኛዎቹ ግልጽነት ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በቀላሉ መልመጃዎቹን ተረድተው እንዲሰሩ ያበረታታል፡፡

ለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ከይዘቱ ጋር ተመጣጣኝነት አይታይበትም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች እኩል ተሳታፊ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ አዘገጃጀት የተማሪዎቹን ዕድሜ፣ደረጃ፣ ችሎታና ዳራ ከግንዛቤ ባስገባ ሁኔታ የተዘጋጁ በመሆናቸው ተገቢ መልስ መስጠት ይችላሉ፡፡

## 5.3 አስተያየት

ለመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች፡- በመጽሐፉ ውስጥ ለክሂል መልመጃዎች ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል የመለማመጃ ጥያቄዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገበሩ የተሟላ መረጃ የሚሰጡ የተካተቱ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ስለመልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ "የሚከተሉትን አሟሉ፡፡" የሚሉ ትዕዛዛትን ያዘሉ ሲሆኑ ምላሻቸውም በጽሁፍ ይሁን በቃል ያልታወቁ መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚገኙ የትንተናው ውጤት ያብራራል፡፡ በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሁሉም አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ምላሽ ስለሚሰጥባቸው በተሟላ ሁኔታ መመሪያዎች እንዲኖራቸው ቢደረግ የተሻለ ነው፡፡ እንዲሁም በንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የቀረቡት ተግባራትና የተሰጠው ጊዜ ተመጣጣኝ አለመሆኑን የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች የሚያዘጋጁትን የይዘት ስፋት ከጊዜው ጋር የተመጣጠነ ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል፡፡

ለጥናት አድራጊዎች፡- ተመራማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ በስፋት ቢያጠኑ ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች፣ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሁም ለቋንቋው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ እና የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያስችሉ አጥኝዋ ታምናለች፡፡

በመልመጃዎቹ ስር የሚካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ጽሑፉን ደጋግመው እንዲያነቡ የሚገፋፉ ሆነው ቢዘጋጁ ተመራጭነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የራሳቸውን የአነባበብ ስልት ተጠቅመው ምንባቡን የመረዳት፣ የመተርጎም፣ የማብራራት፣ የማጠቃለል እና ሌሎች ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት መንገድ የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡

## ዋቢ መጽሐፎች

ሀጎስ ካህሳይ ።(2009)። "ለሰባተኛና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የመምህራን አተገባበር ፍተሻ"። ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተዘጋጀ ጥናት። አዲስ አበባ (ያልታተመ)

ተስፋዬ ሽዋዬ ።(1995) ። "በ1990 ዓ.ም በተዘጋጁ የትግራይ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት ተገቢነትና አቀራረብ"። አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጹሁፍ (ያልታተመ)

ተስፋዬ በቀለ። (1993)። በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለስምንተኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፈፊት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ ለአማርኛ ማስተማሪያ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ( ያልታተመ)

ትዳስ አይነኩሉ ።(2009)። "የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የምንባቦች አመራረጥና አደረጃጀት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት ተገቢነት።"ደብረማርቆስ ዩኒቨርሰቲ (ያልታተመ)

አፀደ ውድነህ ።(1999)።"በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አቀራረብ ስልት ፍተሻ አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ"። ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ። (2009)። የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር። አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ይታያል ወርቁ። (2003)።‹‹ የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ። በቡሉን ወረዳ በተመረጡ ሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት›› ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

Atkins J,etail. (1996).Skill development metrology part 2 A.A U development of forign language and literature.

Celce Murcia,M(Ed).1991. Teaching as a second or foreign language (2nd ed) Bosten፡ Hicinle publisher Ltd.

CresWell, J.W (2012). Educational, Research, Planing, Conducting and Evluating quantitative and qualitative research.(4th ed). Pearson Education, INC.

Davies,F(1995).introducing reading. London: pengiuirn group

Grellent,,f.1991Developing reading skills.A practical guide to reading comprehensive.

Grellent.(1981) Developing reading skills: A partical Guide to reading comprehension exercises, combridge: university press.

Hutchison,j. and Torres,E.(1994).The text book as agent of change. Hong kong:Long man group LTd.

Lindsay and knight.(2006).learning and teaching English.Oxford University press.

M.C Donough,J and C, Show .(2003).Materials and methods in ELT.Second edition oxford; Blackwell.

Nunan,D.(1989).Designing taskes for communicative class room.new york; combride university press.

Nuttal,C.(1982).Teaching reading skills in foreign language.London; long man.

Nuttal,C.(1996).Teaching reading skills in forign language.oxford: Heinemann WF. Publishing.

Rivers, W,M.(1981).TEACHING foreign language skills. Chicago; university of Chicago; university press

Richard,jc.(2001)Curriculum development in language teaching .cambrige: University press.

Sheldon,L.(ed). (1987). EIT text book and develop ment. London,Eastern press LTD

*Ur.penny.(1996).Accurse in language teaching theory and practice.Cambridge, cup.*

*Williams.E. (1984).Reading in the class room. London: macmillan, Ltd.*

Williams.E. (1990).Reading in the class room. London: macmillan, publisher ltd.

Williams,E. (1993). "First and second language reading proficiency of year 3,4&6 children in Malaawi and Zambia" Journal of reading in a foreign language. Vol. Lono.L.PP.915-930.s.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ2013 ዓ/ም ወሰነ ትምህርት በሚዛን-ቁጥር ሁለት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብና አዘገጃጀት በተመለከተ በመምህራን የሚሞላ የቃለ መጠይቅ

ውድመምህር/ት

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና ዓላማ በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አቀራረብና አዘገጃጀት ፍተሻ በሚል ርዕስ ለተዘጋጀ ጥናታዊ ጽሑፍ በሚዛን-ቁጥር ሁለት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን መረጃ ለመሰብሰብ ታስቦ ነው፡፡ ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ በመጠይቁ የተካተቱትን ጥያቄዎች በጥሞና በማዳመጥ ተገቢ የሆነ ምላሽ በመስጠት ይተባበሩኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ጊዜዎን መስዋዕት በማድረግ ለሚያደርጉልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

መጠይቁ ክፍት መጠይቅ ሲሆን ተተኳሪውን መጽሐፍ በተመለከተ በሰነድ ፍተሻው ካገኛቹት መረጃ በመነሳትም ሆነ ስታስተምሩ ከልምድ ባገኛቹት መነሻ በማድረግ ለመጠይቁ ምላሽ ይሰጡን ዘንድ በድጋሚ ትብብሮን እንጠይቃለን

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች |
|---|---|
| 1 | በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ |
| 2 | ይዘቶቹ የአንብቦ መረዳትንና የተለያዩ የቋንቋ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶችን አሟልቶ የመያዝ ሁኔታ |
| 3 | መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ<br>ለክሂል መልመጃዎች ግልጽ የሆኑ መመሪያዎች የመቅረብ ሁኔታዎች |
| 4 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ ለማድረግ ያላቸው አቅም |
| 5 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የማንበብ ክህሎት ለማዳበር ያላቸው እገዛ |

| | |
|---|---|
| 6 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት |
| 7 | በየክፍለ ጊዜው የተሸነሸነው ይዘት ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣመ መሆኑ |
| 8 | በመጽሐፉ ውስጥ በየምዕራፉ የቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ጥያቄዎች ተካተው መገኘታቸው |
| 9 | የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ይዘት ከንባብ ክህል ጋር ያለው ትስስር |
| 10 | የክሂል መልመጃዎቹ ተማሪዎች በውይይት እንዲሰሩ የሚጋብዝ መሆኑ |